# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ መግለጫ

፱ ቤት አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፫ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ‹‹ከቤተ ክርስቲያን ተወግዘው በተለዩ ሰዎች አመላለስ ጉዳይ›› በሚል ርእሰ ጉዳይ ውይይት ተካሄደ፤

*በምኒልክ ብርሃኑ*

በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሲያገለግሉ የነበሩና በኑፋቄ አስተምህሮታቸው ከእናት ቤተ ክርስቲያን ተወግዘው የተለዩ ሰዎች መመለስን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰባክያንና ዘማርያን ኅብረት አዘጋጅነት ማክሰኞ ጥቅምት ፴/፳፻፲፬ ዓ.ም ‹‹ከቤተ ክርስቲያን ተወግዘው የተለዩ ሰዎች አመላለስ ጉዳይ›› በሚል ርእስ ውይይት ተካሄደ፡፡



**ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ**

ለውይይቱ መነሻ ሐሳብ ያቀረቡት ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ ‹‹ለሚመለሱ ሰዎች ምን ልናደርግ ይገባል?›› እና ‹‹ምልሰትና አገልግሎት›› በሚሉ ሁለት ፈርጆች ዳሰሳ አቅርበዋል፡፡በዚህም ከተሐድሶ ፕሮቴስታንት ወደ ኦርቶዶክስ የመመለስ ዓለማቀፋዊ ሂደቶች ምን እንደሚመስሉና በዚህ ሂደት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት ሰዎች ገጥመዋት እንደነበር ገልጸዋል፡፡ጥናት አቅራቢው ለመዳን የተመለሱት ዘመናቸውን በንስሓ እንዳሳለፉ ሁሉ በመውጣታቸው ምክንያት ያጡትን ዕድል ተመልሰው ለማግኘትና ከውስጥ ሆነው ለመቀሰጥ (ለማስካድ) እንዲመቻቸው በማሰብ የሚመለሱ እንዳሉ በገለጻቸው አንሥተዋል፡፡ዲ/ን ያረጋል አክለውም ማንነታቸውን ሳይለውጡ በአፍኣ ብቻ ‹‹ተመልሰናል›› በማለት ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ ፈትነዋት እንደነበርና በአሁኑ ጊዜም ‹‹ተመልሰናል›› ለሚሉም ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግም አስረድተዋል፡፡

ዲ/ን ያረጋል አያይዘውም ለሚመለሱ ምን ማድረግ ይገባል? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መሆኑን አንሥተው፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን አስተምህሮ በትክክል ያልተረዱ፣ ስሕተታቸው መሠረታዊው የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በመሆኑ፤ ከዚህ ስሕተት እንዲነጹ ያልተቋረጠና ተከታታይነት ያለው ኦርቶዶክሳዊ ሥልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ተናግረዋል፡፡የኑፋቄ ስብከታቸውንና የጻፏቸውን የሐሰት ትምህርቶች ቀድመው ባስተላለፉበት ልሳንና መንገድ ማውገዝ ይገባቸዋል ሲሉም አጽንዖት ሰጥተዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ያወገዘቻቸው በጉባኤ እንደመሆኑ መጠን መመለሳቸውንም መነገር ያለበት በማኅበራዊ ሚዲያ ሳይሆን በጉባኤ መሆን እንዳለበት አሳስበው፤ በእነርሱ የኑፋቄ ትምህርት ምክንያት የወጡና የጠፉ ምእመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን የመመለስ ኃላፊነት አለባቸው ሲሉም አስገንዝበዋል፡፡ከዚህ በፊት ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ወጥተው የተመለሱ ሰዎችን በችኮላ ወደ መድረክ በማውጣት ችግር ተፈጥሮ እንደነበር ያስታወሱት ጥናት አቅራቢው በተመሳሳይ ቤተ ክርስቲያንን ሲያንቋሽሹና ሲሰድቡ የነበሩ አካላት ሲመለሱ በነበሩበት ክብርና መዓርግ፣ ከመድረክ ወደ መድረክ መመለስ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ሥጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም የቀረበውን ገለጻ መነሻ በማድረግ አስተያየታቸውን የሰጡት የጉባኤው ተሳታፊዎችም፣ በአሁኑ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡ አንዳንዶች ምእመኑን ለመቀሰጥና የተሐድሶ ፕሮቴስታንት እንቅስቃሴን ለማስፋፋት መሆኑን በመረዳት ሰፊ የግንዛቤ ሥራ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡መወገዛቸውን የተናገረችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እስከሆነች ድረስ መመለሳቸውንም መንገር ያለባት ራስዋ ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን፤ ኦርቶዶክሳዊ የመገናኛ ብዙኃንን በመጠቀምና የሚመለከታቸውን አካላት በመጋበዝ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ እንደሚያስፈልግ፤ እንዲሁም እንዲህ ዓይነት መድረኮችን ከከተማ ወደ ክልሎች በማስፋፋትና በማካሄድ ከሊቃነ ጳጳሳት፣ ከየአህጉረ ስብከቶች እና ሰንበት ት/ቤቶች ጋር አብሮ በመሥራት ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ አስተያየቶችን በመስጠት ውይይቱ ተጠናቋል፡፡

# ማኅበረ ቅዱሳን ሥነ ሥዕል ክፍል “የብርሃን ሰሌዳዎች” በሚል ርእስ የሥዕል ዐውደ ርእይ ተካሄደ





*የሥዕል ዐውደ ርዕይ በተካሄደበት ወቅት*

*በምኒልክ ብርሃኑ*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ ማኅበረ ቅዱሳን ሥነ ሥዕል ክፍል ከጥቅምት ፳፯ እስከ ኅዳር ፬/፳፻፲፬ ዓ.ም ድረስ ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላትን የሚዳስስ “የብርሃን ሰሌዳዎች” በሚል የሥዕል ዐውደ ርእይ ተካሄደ።

በሥዕል ዐውደ ርእዩ መዝጊያ ላይ የማኅበረ ቅዱሳን ሥነ ሥዕል ክፍል በቀለም ቅብ እና በግራፊክስ ዲዛይን ለዐሥር ወራት ያህል ሲያሠለጥናቸው የነበሩ ሠልጣኞች ለሁለተኛ ጊዜ ማስመረቁን የሥነ ሥዕል ክፍሉ አስተባባሪ ሠዓሊ ዘሪሁን ገ/ወልድ በምረቃው ወቅት የገለጹ ሲሆን በዐውደ ርእዩ ለእይታ የቀረቡት ቅዱሳት ሥዕላትም በተመራቂ ተማሪዎች እንደተሣሉ ተናግረዋል።

ተማሪዎቹ በየአጥቢያቸው ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ላይ በቤተ መቅደስ ውስጥ በሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላትን በተመለከተ ዐውደ ጥናት አቅርበዋል።በጥናቱም በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላት ከኦርቶዶክሳዊ አሣሣል ዘዴ፣ ከኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ እንዲሁም ከአቀማመጥና ከስያሜ አንጻር በቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችና የመፍትሔ አሳቦች ተመላክተዋል።

በተጨማሪም በሥዕል ዐውደ ርእዩ ላይ በተመራቂ ተማሪዎች የተሠራ ORNAMENT REALITY (OR) የተሰኘ የሥዕል ቴክኖሎጂ የተዋወቀ ሲሆን አገልግሎቱም ስለ ሥዕሉ ሙሉ መግለጫ በመስጠት ማን እንደሣለው፣ መጠኑን፣ የተሠራበትን ቁስ እና የቅዱሳኑን ሙሉ ታሪክ በቀላሉ ማስረዳት እንደሚያስችል ተገልጿል።ቴክኖሎጂው ቅዱሳንን በተመለከተ ሙሉ መረጃ የሚያቀብል በመሆኑም “የብርሃን ሰሌዳዎች” የሚል ስያሜ እንደተሰጠው ተገልጿል።

ለስምንት ቀናት ክፍት ሆኖ በቆየው በዚህ የቅዱሳት ሥዕላት ዐውደ ርእይ ሰማንያ ሠዓልያን የተሳተፉበት በቀለምና በዲጂታል የአሣሣል ዘዴ በብራና፣ በሸራና በሰሌዳ (በገበታ) ላይ የተሣሉ ሥዕላት ለእይታ ቀርበዋል።

# ወቅቱ ክርስትናችንን በተግባር የምንገልጽበት ነው

ሀገረ እግዚአብሔር እየተባለች የምትጠራው ሀገራችን ኢትዮጵያ ስለ ሀገር እና በውስጧ ስለሚኖሩ ሕዝቦች ሰላም ዘወትር በቅዳሴዋ የምትጸልየው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በሰላም መደፍረስ ምክንያት ሲታወኩ ቆይተዋል::ዛሬም እየታወኩ መሆናቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው::በተለይ በየትኛውም የሰላም መደፍረስ ውስጥ ሁሌም የመጀመሪያዋ ተጎጂ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በሀገር ውስጥ ባለው የሰላም እጦት ምክንያት የመጀመሪያዋ የጥቃት ሰለባ ሆና ቆይታለች ዛሬም በዚያ ውስጥ ናት::

በየጊዜው መልካቸውን እና አጀንዳቸውን በሚቀያይሩ ፀረ ሰላም ኃይሎች፣ የእርስ በርስ ግጭቶች ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ መከራን እየተቀበለች ትገኛለች::በሃይማኖታዊ ግጭቶች፣ በጎሣ ልዩነቶች፣ በጦርነቶች ውስጥ የችግሮቹ ሁሉ ዱላ የሚያርፈው በቅድሚያ በቤተ ክርስቲያንና ልጆቿ ላይ ነው::ይህ በመሆኑም የተለያዩ ችግሮች በሀገሪቱ ውስጥ በተነሱ ቁጥር አብያተ ክርስቲያናት ሲዘጉ፣ ሲቃጠሉ፣ ሲዘረፉ እንዲሁም ካህናትና ምእመናን ሲገደሉ፣ ቤት ንብረታቸው ሲዘረፍ እና ከየቀያቸው ሲሰደዱ ኖረዋል አሁንም በዚያ ሰቆቃ ውስጥ ናቸው::

ከአንደኛው አካባቢ አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል ሲባል በሌላኛው የሀገሪቱ ክፍሎች እንደ ሰደድ እሳት የሚዛመተው ዘርፈ ብዙ ግጭት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን ብርቱ ፈተና እየሆነ ነው::በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን የዕለት ከዕለት አገልግሎቷን መስጠት አልቻለችም::ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደርስባቸው አብያተ ክርስቲያናት በመቃጠላቸው፣ በመዘረፋቸው አሊያም በመዘጋታቸው ምክንያት ምእመናን የሚጸልዩበት፣ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣ የሚጠመቁበት በማጣት ችግር ውስጥ ናቸው::

የደቡቡ ሰቆቃ ሳይበቃ የክርስትናው ማእከል ነው በሚባለው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እየተካሐሄደ ባለው ግጭጥ ውስጥ የትኛውም ወገን ሆነ ቦታ ላይ ሚዛን የሚደፋው ተጎጂ ቤተ ክርስቲያን እና ምእመናን ላይ ነው::

የክርስትና ማእከል ነው በሚባለው የሰሜኑ ክፍል ምን ያህል አብያተ ክርስቲያን ተዘግተዋል? ምን ያህሉስ ተዘርፈው ተቃጥለዋል? ስንት ክርስቲያን ሕይወቱን ገብሯል? የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ዕጣ ፈንታስ ምን ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የሚጠበቅ ነው::

ስንት ቤተ ክርስቲያን ሲቃጠል፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲወድሙ አሊያም፤ ክርስቲያኖች ሲጠፉ ነው የመከራው ብዛት ውስጣችን ዘልቆ የሚሰማን? የሀገርን አንድነት ፣ ዳር ድንበሯን አስጠብቀው ለትውልድ ያቆዩ ታላላቅ የሀገር መሪዎችን ያፈራች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ በዐውደ ምሕረቷ ዘወትር ሰላምን የምትሰብክ በቅዳሴዋ ‹‹ስለ ቤተ ክርስቲያን ጸልዩ›› ስትል የኖረች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አብያተ ክርስቲያን ስብሐተ እግዚአብሔር እንዳይደርስባቸው ተዘግተዋል::በዚህ ሁሉ ትርምስ ውስጥ ነገስ ወዴት እያመራን ነው ብሎ በብርቱ የሚጠይቅ ፣የሚከታተል ተቆርቋሪ ያስፈልጋታል::

ቤተ ክርስቲያን በደረሰባት ጉዳት ሁሉ  ጊዜያዊ እሳት ከማጥፋት የዘለለ ቀጣይ ነገር ባለመኖሩ ከቁስሏ ሳታገግም ዛሬ ደርሳለች::ሁሉም ሰው ሊስማማበት የሚገባው ሐቅ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር ክርስቲያኖች መኖራቸው የግድ ነውና ከሞት ለተረፉት ለሕይወታቸው፣ ለክርስትናቸው፣ ለኑሯቸው ልንጨነቅ፣ መፍትሔ ልንፈልግ ይገባል:: ያዘኑትን በማጽናናት፣ የተጎዱትን በመርዳት፣ የተፈናቀሉትን በማሰባሰብ ይልቁንም አጽናኝ የሆነው ቃለ እግዚአብሔርን በማስተማር ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም በፊት ልትሠራው ይገባል:: አንዱ ሌላውን በመርዳት የተሻለው በማገልገል ክርስትናን እና ክርስቲያኖችን ለመታደግ የሁላችንም መንፈሳዊ ትጋት ወሳኝ ነው::

ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ለመጸለይ፣ ለማገልገል ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋል:: ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያን እንደሚያስፈልጓት ሁሉ፤ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቲያኞች ታስፈልጋለችና የተዘጋው የሚከፈትበት የተቃጠለው የሚታደስበት ላይ አጥብቆ መሥራት አስፈላጊ ነው::ይልቁንም ዛሬ  ከመልካም ዜናዎች ርቀን እና ብዙ ልብን የሚያሳዝኑ መርዶዎች በምንሰማበት ጊዜ ላይ ነንና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን ልንጨነቅ ይገባናል::

አሁን ወቅቱ እያንዳንዳችን በተናጠል ቆመን ችግራችንን የምንገልጥበት ሳይሆን እንደ ሀገር ሁላችን ያዘንበት እንደ ኢትዮጵያ ሀገሪቱ ችግር ላይ የወደቀችበት ወቅት ነው:: ስለዚህ ጊዜው ክርስትናችንን በተግባር የምንገልጥበት፤ አንዱ ላንዱ የሚያስብበት፤ ለመረዳዳት፣ ለመተጋገዝ የምንተጋበት ወቅት መሆኑን ልብ ልንል ይገባል::

እስከ አሁን ያለው ተሳትፎ እንዳለ ሆኖ አሁንም መንግሥት እንደ መንግሥት የዜጎች የመኖር ዋስትና እና ሰላም በሚሆኑበት ጉዳይ ላይ በትጋት መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ቤተ ክህነት አብያተ ክርስቲያናትን፣ ምእመናንን ከሚደርስባቸው ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ለመታደግ ከመንግሥት ጋር በቅርበት መሥራት፣ ችግሩን አጥንቶ መፍትሔ መፈለግ ይጠበቅበታል፣ አባቶች ከጥንት ጀምሮ ሀገር እና ቤተ ክርስቲያንን በጠበቁበት መንገድ ስለ አንድነት፣ ስለሰላም በመስበክ በማስተማር፣ የሚገሰፀውን በመገሰፅ የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም እንደ ክርስቲያን የሰዎች ሞት ሊገደን ፣ የቤተ ክርስቲያን መሰደድ ሊያንገበግበን ይገባል፡፡ አንዱ ስለሌላው ግድ ሊለው አንዱ የሌላውን ሸክም በመሸከም እውነተኛ ክርስቲያኖች ልንሆን ይገባል፡፡

የሰላም ተምሳሌት፣ የሰላም ወደብ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የነበራት ሰላም እንዲቀጥል ዛሬ ላይ ተግተን ልንሠራ፣ እንደ አንድ የእምነት ሰው በብርቱ ልንጸልይ፣ ልንረዳዳ ወቅቱ የሚጠይቀን ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡

**ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደርስባቸው አብያተ ክርስቲያናት በመቃጠላቸው፣ በመዘረፋቸው አሊያም በመዘጋታቸው ምክንያት ምእመናን የሚጸልዩበት፣ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣ የሚጠመቁበት በማጣት ችግር ውስጥ ናቸው፡፡**

# ‹‹የቤተ ክርስቲያኗን መዋቅራዊ አሠራር አጠናክረን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ብላ እንድትታይ በመልካም አርአያነት ጠንክረን እንሠራለን ››

(የ፵ኛው የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተሳታፊዎች)

## •‹‹የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤው ፵ ዓመታት ቢያስቆጥርም የዕድሜውን ያህል የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስፋፋት አልቻለም››

(ምእመናን)

በሻምበል ጥላሁን

*የተከበራችሁ አንባብያን ባለፈው የሪፖርታዥ ዓምድ እትማችን ፵ኛው የሰበካ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ የተነሣውን ባለ ፳ ነጥብ የአቋም መግለጫ ማውጣታችን ይታወሳል።በዚህ እትም ደግሞ ምእመናን የሚያነሷቸውን መልካም ጎን እና ቅሬታዎች እንደሚከተለው አቅርበናል ተከታተሉን፡-*

ከጥቅምት ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ ለሦስት ቀናት በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ጽርሐ ተዋሕዶ አዳራሽ የተካሄደው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ባለ ፳ ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት መጠናቀቁ ይታወቃል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በ፳፻፱ ዓ.ም ለዐራተኛ ጊዜ ተሻሽሎ በወጣው ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፳ ላይ እንደተገለጸው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዓላማ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅና አገልግሎቷም የተሟላ እንዲኾን ማድረግ፤ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች በሐዋርያዊ ተግባር ማደራጀትና ችሎታቸውንና ኑሯቸውን ማሻሻል፤ ምእመናንን ማብዛትና በመንፈሳዊ ዕውቀት ጕልምሰው፣ በምግባር በሃይማኖት ጸንተው በክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖሩ ማድረግ፤ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ማሻሻልና በማናቸውም ጉዳይ ራሳቸውን ማስቻል ነው በማለት ተቀምጧል።

ይህንን መንፈሳዊ ዓላማ ለማስፈጸም የተዋቀረው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤም የእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች፤ ከየመንበረ ጵጵስናው የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት እና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያ ኃላፊዎች ጋር በአንድነት ተሰባስበው የሚመሠርቱት ጉባኤ ሲኾን፣ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዳለውና ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባ እንደኾነ በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፵፮ ላይ ተደንግጓል።

ከዚህም በተጨማሪ በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፵፯ ላይ በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ዓመታዊ ጉባኤው ላይ ፓትርያርኩ ርእሰ መንበር፤ ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ምክትል ሊቀ መንበር፤ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት አባላት፤ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ አባልና ጸሐፊ፤ የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባል፤ የአህጉረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች አባላት፤ ከየአህጉረ ስብከት መንፈሳውያን አስተዳደር ጉባኤያት የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናን እና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች አባላት፤ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች አባላት ሆነው የሚሳተፉበት ታላቅና ወሳኝ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው።

ጉባኤው የአህጉረ ስብከትን ሪፖርቶችና ዕቅዶች ከሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ እና ተመካክሮ ውሳኔ ማሳለፍ፤ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማጠናከር ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቶች፣ የካህናት፣ የሰባክያንና የሰንበት ት/ቤት መምህራን ማሠልጠኛዎች እንደዚሁም የልማትና በጎ አድራጎት ተቋማት በሀገረ ስብከት እና በማእከል ደረጃ እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ማድረግ ነው።

ይህ ለቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ካሁን ቀደም ይደረግ እንደነበረው ሁሉ፣ በዘንድሮው ዓመትም ጥቅምት ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጽርሐ ተዋሕዶ አዳራሽ ተካሒዷል።

ከተመሠረተ ከ፵ ዓመታት በላይ ያስቆጠረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ የተለያዩ ውጣ ውረዶችን እያለፈ ዛሬ ላይ ደርሷል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስተያንን ሐዋርያዊ አገልግሎት በማስፋፋት፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮቿን መዝግባ ይዛ ሥምሪት እና ምደባ እንድትሰጥ፣ ምእመናኖቿ ችሎታቸውንና ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ፣ ምእመናንን ለማብዛትና በመንፈሳዊ እውቀት ጎልምሰው፣ በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ ለማድረግ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ለማሻሻልና በሚያስፈልጋት ማንኛውም ጉዳይ ራሷን ለማስቻል ጉባኤው የሚጠበቅበትን ተውጥቷል? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ የበርካታ ምእመናን መወያያ ከሆነም ውሎ አድሯል። ‹‹የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ የዕድሜውን ያህል ለቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ እድገት የሚጠበቅበትን አልተወጣም ብለው ከሚያምኑት

ወገን ነኝ›› ይላል ከጉባኤው ተሳታፊዎች አንዱ ዲያቆን ኢንጂነር ዘለዓለም፡፡

ዲያቆን ኢንጂነር ዘለዓለም ዓለምነው የአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ምእመን ነው፡፡ዲያቆን ዘለዓለም በሰንበት ትምህርት ቤት በልዩ ልዩ ክፍሎች ማገልገሉን፤ በአጥቢያው ሰበካ ጉባኤም ተሳትፎ እንደነበረው ያስታውሳል፡፡ በዚህ ጉባኤም እድሉን አግኝቶ ‹የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ መታደሙን የሚናገረው ዲያቆን ዘለዓለም ጉባኤው ሰፊ ሽፋን የሚወስደው ሪፖርት በማንበብና በማሰማት ነው ይላል፡፡የታተመውን ሪፖርት በማንበብ አብዛኛው ጊዜ ይባክናል የሚለው ዲ/ን ዘለዓለም፤ ጉባኤው ተግባራዊ በሚደረግና መሬት ላይ ወርዶ በሚሠራ ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መወያየት ይገባ ነበር ይላል፡፡

ሌላው አስተያየት ሰጪ አቶ ደበበ ኃይለ ገብርኤል ሲሆኑ የሕግ ባለሙያ፣ ጠበቃና በሰብአዊ መብቶች ላይ ተመራማሪ ናቸው፤ አቶ ደበበ አሁን በሚኖሩበት ሲኤም ሲ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ምእመን ናቸው፡፡‹‹የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን መጠበቅና አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን በማድረግ፤ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች በሐዋርያዊ ተግባር ማደራጀትና ችሎታቸውንና ኑሯቸውን በማሻሻል ይነስም ይብዛ የማይተካ ሚና ተወጥቷል፤ እየተወጣም ነው ብለው ያምናሉ፡፡

ይሁን እንጂ ይላሉ የሕግ ባለሙያው በሰበካ መንፈሳዊ ጠቅላላ ጉባኤያት የሚወሰኑ ጉዳዮች ታች ወርደው በየደረጃው ለሚገኙ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያት ለአፈጻጸም እና ለግንዛቤ እንዲደርሱ አለመደረጉን፤ በአንዳንድ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤዎች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን አጣርቶ የመፍትሔ እና የውሳኔ ሐሳብ ማቅረብ ላይ ሰፋ ያሉ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ ያስረዳሉ፡፡

ጉባኤው ሰፊ ጊዜና ሽፋን የሚወስደው ሪፖርት በመስማት ነው በሚለው ሐሳብ ከዲያቆን ዘለዓለም ጋር እንደሚስማሙ የሚናገሩት የሕግ ባለሙያው፤ የሰበካ መንፈሳዊ አጠቃላይ ጉባኤያት የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ጉባኤዎቹ ሪፖርቶች ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን ችግር ፈቺ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የጠነከረ ውይይት ቢያደርጉ መልካም ነው ሲሉም ያስረዳሉ፡፡

እንዲሁም ወይዘሮ ሐና የሺጥላ የኮልፌ ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ገዳም ምእመን ሲሆኑ፤ በኮልፌ ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅም በነገረ መለኮት ዲፕሎማ አግኝተዋል፡፡ ወይዘሮ ሐና ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከተለመደው የዕለት ከዕለት አሠራር ውጪ ወጥተው እንደ አኃት አብያተ ክርስቲያናት የተማሩ ምእመናኖችን በተለያዩ የአገልግሎት መስኮች ሲያሳትፉ አይስተዋልም ሲሉ አስተያታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ወይዘሮ ሐና አያይዘውም ‹‹ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ በሚገኙ በአኃት አብያተ ክርስቲያናትም በእንግሊዘኛው አጠራር /ሪሽ ካውንስል/ በሚል ስያሜ እየተሠራበት የሚገኝ ዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ነው›› ይላሉ፡፡ ‹‹የዚህ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ /ሪሽ ካውንስል/ መዋቅርና አሠራር ዋና ሥራውም ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች በምእመናን ላይ የሚያስከትሉትን ተፀዕኖ እና መልካም አጋጣሚ ባገናዘበ እና የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ አገልግሎት ዘመኑን በዋጀ መልኩ ማስፋፋት ነው›› በማለት ያብራራሉ፡፡

ለዚህም ዋና ሥራቸው የሚያስፈልገውን ዐቅም መፍጠርና ማጠናከር፣ የምእመናን ችግር መፍቻ እንዲሆኑ ለማድረግ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢያዊና የምእመናንን አኗኗር ሁኔታዎች ለመለወጥ ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መዋቅርና አሠራር በመዘርጋት ተጨባጭና ነባራዊ ሁኔታዎችን የተከተሉ የሕግና የመዋቅር ማሻሻያዎችን እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ፡፡በእኛም ቤተ ክርስቲያን ቃለ ዓዋዲ በ፳፻፱ ዓ.ም ለዐራተኛ ጊዜ መሻሻሉን የሚያስታውሱት ወይዘሮ ሐና ቃለ ዓዋዲው ምእመናን እንደ ሙያና ደረጃቸው እንዲሳተፉ አሠራር ቢያስቀምጥም በየአጥቢያው የሚገኙ ሰበካ ጉባኤያት ግን አሠራራቸው ከቃለ ዓዋዲው በተቃራኒ ነው ይላሉ፡፡

እንደ ወ/ሮ ሐና ዛሬ ላይ በተለይም ሙስና የቤተ ክህነቱና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ዋና መለያ ጠባይ እየሆነ ነው፡፡ችግሩም ቤተ ክህነቱን ጥፍንግ አድርጎ የደብር አስተዳዳሪነት፣ የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅነት፣ የመመሪያ ኃላፊነት፣ የውጭ የትምህርትና የሥራ ዕድል ያለ ጉቦና መማለጃ የማይገኙ መሆናቸው የአደባባይ ምሥጢር መሆናቸውንም ያስረዳሉ፡፡

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መዋቅር ከተዘረጋ ግማሽ ምእተ ዓመት የተጠጋው ነው የሚሉት የሕግ ባለሙያው አቶ ደበበ የቤተ ክህነቱና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ አሠራሮች የመዋቅር ማሻሻያ ሲያልፍም ያልነካቸው፣ መምሪያዎችና ክፍሎች፣ ድርጅቶችና ተቋማት ያለ ጥናት በአንድ ቀን ውሳኔ ሲከፈቱና ሲዘጉ የሚኖሩበት፣ሀገሪቱ ካይዘንንና ቢፒ አር የመሳሰሉ አሠራሮችን ስትተገብር ከቦታው ያልተነቃነቀ መዋቅር ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ምን ያህል የሰው ኃይል አላችሁ? በምን ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋችኋል? በአንድ ደብር ስንት ሰው መኖር አለበት? ቢባል ቤተ ክህነት ሆነ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መልስ የላቸውም የሚሉት አስተያየት ሰጪው ኮምፒውተር በሌለበት አጥቢያ የኮምፒውተር ጸሐፊ፣ ለአንድ አጥቢያ አራት የስብከተ ወንጌል ኃላፊ፣

የአብነት ትምህርት ቤት ለሌለበት ደብር የአብነት ትምህርት ተቆጣጣሪ የሚመደበው መዋቅሩ ያልተጠና የዘመድ አሠራር የተበተበው ስለሆነ ነው በማለት ያብራራሉ።

ቤተ ክርስቲያንን ለሌላው አርአያ ያደርጋታል፤ ሐዋርያዊ አገልግሎቷንም ያሳልጥላታል ተብሎ የተዋቀረው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በችግር መጠቀስ የለበትም ይላሉ።ከዚህ በፊት የፍትሕ አካላቱ ቤተ ክህነትን የሚመለከቱ ክሶች እየበዙ መምጣታቸውን ለቅዱስ ሲኖዶስ ማሳሰቢያ ሰጥተው እንደነበር እንደሚያስታውሱ የሚገልጹት የሕግ ባለሙያው የሰብአዊ መብት ኮሚሽንም ከሚደርሱት አቤቱታዎች አብዛኞቹ ቤተ ክህነቱን የሚመለከቱ መሆናቸው መስማቱን ያክላሉ።የቤተ ክህነቱ ግቢም ሥራ በሚሠሩ ሰዎች ሳይሆን አቤቱታ ይዘው ከመላዋ ሀገሪቱ በሚመጡ ባለጉዳዮች የተሞላ ነውም ይላሉ።

በየአጥቢያውም ተአምርና ገድል ሳይሆን የገንዘብ መጥፋት፣ የቦታ መሸጥ፣ የዘመድ ቅጥር፣ የሙዳየ ምጽዋት መሰረቅ ነው የሚሰማው የሚሉት ደግሞ ዲያቆን ዘለዓለም ናቸው።ቀድሞ የሬዲዮና የጋዜጣ፣ የመጽሔትና የፊልም ጀማሪ የነበረች ቤተ ክህነት አሁን ያላት ሚዲያ ዘመኑን የዋጀ አይደለም ይላሉ በቁጭት።

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፻፲፯ኛው ፓትርያርክ የነበሩት ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ በዘመናቸው ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከሠሯቸው ሥራዎች አንዱ ዘመናዊ የሆነ የኦዲዮ ቪዠዋል ማእከል ባለቤት ማድረጋቸው ነው የሚሉት ዲያቆን ዘለዓለም ኮፕቲክ ቴሌቭዥንን፣ አጋፒያና ክርስቲያን ቲቪ የተሰኙ የቤተ ክርስቲያኒቱን የዕለት ተዕለት ጉዳዮች የሚዘግቡ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ተቋቁመዋል በማለት ያስረዳሉ።ኮፕቶች ከዘመናዊ ሚዲያዎች በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኒቱን፣ የአገልጋዮቹንና የምእምናንን ሕይወት የሚያሻሽሉ በርካታ የንግድ ተቋማት ባለቤትም ናቸው።የቤተ ክርስቲያኒቱ አደረጃጀት እና አወቃቀር ጠንካራ ነው፤ ይህ ቁጭት ሊፈጥርብን ይገባል በማለት ይናገራሉ።

እንደ ዲያቆን ኢንጂነር ዘለዓለም ገለጻ በየዓመቱ በጥቅምት የሚካሄደው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በዋናነት መወያየት ያለበት ቤተ ክርስቲያናችን አሁን የት ላይ ናት? ምን ችግሮችን እያስተናገደች ነው? አህጉረ ስብከቶች ለችግሮች ምን መፍትሔ አስቀመጡ? ጠቅላይ ቤተ ክህነትስ? ቅዱስ ሲኖዶስ ምን ሠራ? መንፈሳዊ ኮሌጆቻችን ደቀ መዛሙርትን እንዴት ነው እያሠለጠኑ ያሉት? የሠለጠኑትስ በተማሩት ትምህርት ፍሬ ማፍራት ችለዋል ወይ? በመንፈሳዊ ኮሌጅ የተመደቡት መምህራንስ ለኮሌጆቹ ይመጥናሉ? የሚሉ ጉዳዮች ዋነኛ አጀንዳዎች መሆን ይገባቸዋል ይላሉ።

በተለይም የአብነት ተማሪዎችና መምህራን ቁጥር መቀነስ መንሥኤውና መፍትሔው ምን ድን ነው? ቅዱሳት ገዳማት በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ምን ይጠበቃል? በትልልቅ ከተሞች የሠርክ ጉባኤያት ለምን ተዳከሙ? በውጭ ዓለማት ባሉና በሀገራችን ባሉ ክፍላተ ሀገሮች ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ትምህርት እንዲማሩና የሥላሴን ልጅነት እንዲያገኙ የቋንቋ መምህራንን እንዴት ማፍራት እንችላለን? ገዳማዊ አደረጃጀት እና የመነኮሳት አኗኗር በሚሉት ርእስ ጉዳዮች ላይም ትኩረት ሰጥቶ መምከር ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም በማለት ያስረዳሉ።

የሕግ ባለሙያው ደበበ ኃይለ ገብርኤልም ጉባኤው ሊወያይባቸው ይገባል የተባሉት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው በሰበካ መንፈሳዊ ጠቅላላ ጉባኤያት የሚወሰኑ ጉዳዮች ጊዜ በማይወስድ ሁኔታ ታች ድረስ በመውረድ በየደረጃው ለሚገኙ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያት ለአፈጻጸም እና ለግንዛቤ እንዲደርሱ አሠራር ሊኖር ይገባል ይላሉ።በአንዳንድ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤዎች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን አጣርቶ የመፍትሔ እና የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ትጉህ እና ለችግሮች ገለልተኛ የሆነ እንደ ጉዳዩ ዓይነት የተለያዩ ሙያ ያላቸው ምእመናን የሚሳተፉበት አሠራር መዋቅራዊ እንዲሆን ማድረግ ቢቻል ውጤታማ መሆን ይቻላል በማለትም ያክላሉ።

እንደ ወ/ሮ ሐና የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የራሱን መዋቅርና አሠራር ከማስተካከል፣ በሊቃውንትና በባለሞያዎች የሚታገዝበትን መንገድ ከመፍጠር፣ ውሳኔዎች የሚያስፈጽምበትን ዐቅምና አሠራር ከመዘርጋት መጀመር አለበት። የየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤያትም ሆኑ አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት በሊቃውንትና በባለሙያዎች መደገፍ አለባቸው የሚሉት ወይዘሮ ሐና ሐሳቦች በአንድ ቀን ጉባኤ ተጀምረው ማለቅ የለባቸውም።አስቀድሞ በሊቃውንትና በባለሞያዎች የተመከረባቸው መሆን አለባቸው ሲሉም ጠቅሰዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ በአጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት የሚወሰኑና የሚቀርቡ የመፍትሔ ሐሳቦችን ተቀብሎ የለውጡን ሥራ ከላይ እስከታች ማውረድ ይገባዋል ሲሉ ያክላሉ። ከምእመናንና ከሊቃውንቱ በየጊዜው የሚቀርቡትን ሃሳቦች የሰበካ መንፈሳዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ መሠረት ያለው፣ ለምእመኑ ተስፋ የሚፈነጥቅና የነገውን መንገድ የሚያቀና ውሳኔ ያሳልፍባቸዋል፤ አፈጻጸማቸውም ከወረቀት ይዘላል ብለን ተስፋ እናደርጋለን በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# «አባቴ ከቤት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን እስከምንደርስ ድረስ ያለማቋረጥ ውዳሴ ማርያም እየደገሙ ነበር የሚሄዱት፤»

በሚኒልክ ብርሃኑ

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን በርካታ አስተዋፅዖ አድርጋለች። ካደረገቻቸው አስተዋፅዖ መካከል ቋንቋ፣ ባህል፣ ፊደል፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ትምህርት ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሽ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ለድንቅ ቅርሶቻችን መገኘት፣ ለእልፍ ቅዱሳን መፍለቂያ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ታሪክ ስነዳና እድገት አንድ ክፍል በመሆን አገልግላለች። ለዘመናት በዘለቀው ቁርኝት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ባህል ምንጭ፣ ለታሪኳ ደግሞ መዛግብት በመሆን አገልግላለች።

በዓለማችን ቀደምት ሥልጣኔ ከታየባቸው ጥቂት አገራት መካከል ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ናት። ለሥልጣኔ መነሻዋ ደግሞ ትምህርት ነው። የኢትዮጵያን ቀደምት የሥልጣኔ ውጤቶችን ስናደንቅ፣ በተዘዋዋሪ በጊዜው የነበረውን የትምህርት (የዕውቀት) ሥርዐት ማድነቃችን ነው። ኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፉ እጅግ ጥንታዊ የሆነ መሠረት ነበራት። ይህን አመክንዮ የሚያስረግጡልን፣ በቅርቡ በአኵሱምና በግብፅ ፒራሚዶች ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችና በከርሠ ምድር የተገኙት ማስረጃዎች ናቸው። (ካህሳይ ገ/እግዚአብሔር፣ ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ፣ ገጽ ፳፩) እነዚህ ማስረጃዎች ከዛሬ ሰባት ሺህ ዓመታት በፊት በዳዓማት ዘመነ መንግሥት ጊዜ እንደነበሩና በወቅቱ ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል የጽሑፍ ሥራ ተንሠራፍቶ እንደነበር ያሳያሉ። በየሃ፣ በአኵሱምና በተለያዩ የትግራይ አካባቢዎች በኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነት ከመግባቱ አስቀድሞ፣ በሳባውያን ዘመን በጽሑፍ የታገዘ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንደ ነበር የሚያመላክቱ የጽሑፍ ሥራዎች ተገኝተዋል። በዚህ ወቅት ትምህርት በኢትዮጵያ በስፋትና በጥራት ይሰጥ ስለነበር ከሌሎች አገራት እየመጡ ይማሩ ነበር። ከመጡትም መካከል ሊቀ ነቢያት ሙሴ አንዱ የነበረ ሲሆን መምህሩ ደግሞ ኢትዮጵያዊው ዮቶር እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

ይህ በዘመናት ሂደት ውስጥ ሳይለወጥ እስካሁን የቀጠለው የአብነት ትምህርት፣ በየዘመናቱ በተነሡ ሊቃውንት ይበልጥ እያበበ ዛሬ ድረስ ዘልቋል፤ ዛሬም በገጠሩ ክፍል እንዲሁም በተለያዩ ከተሞች እየተሰጠ ይገኛል። ጥንታዊውን የአብነት ትምህርት በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ላለፉት ዐሥራ ዘጠኝ ዓመታት ሲያስተምሩ የቆዩትንና ዛሬም ድረስ በማስተማር ያሉትን መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴን በዛሬው ዝግጅታችን የቤተ አብርሃም ዓምድ እንግዳችን አድርገናቸዋል። በጥሞና እንድታነቡ በአክብሮት እናሳስባለን።



መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ

**ስምዐ ጽድቅ፡-** አባታችን በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

**መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ፡-** እናንተም ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ እኔን ለመጠየቅ እዚህ ድረስ ስለመጣችሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** አባታችን የት ተወለዱ? እናትና አባትዎስ ማን ይባላሉ?

**መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ፡-** የተወለድሁት በትግራይ ክፍለ ሀገር በውቅሮ ከተማ ሁለት አውላሎ አውራጃ ልዩ ስሙ አብርሀ ወአጽብሐ በሚባል አካባቢ በ፲፱፻፵፮ ዓ.ም ጥቅምት ፳፫ ቀን ነው። አባቴ ርእሰ ደብር ገብረ ሥላሴ ካህሳይ፤ እናቴ ደግሞ ኀሪት ተስፋይ ይባላሉ።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** አስተዳደግዎ ምን ይመስል ነበር ቢገልጹልን?

**መምህር ኀሩይ፡-** ለእናትና አባቴ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ፡፡ እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ከአኀቶቼና ከአክስቶቼ ጋር በመሆን ከብት እየጠበቅሁ ነው ያደግሁት፡፡ በልጅነቴ ጨዋታ እወድ ነበር፤ በተለይ ሩር የሚባለውን ጨዋታ በጣም እጫወት ነበር፡፡ ቤተሰቦቼ ጥሩ ኑሮ የሚኖሩ ስለነበሩ፣ እንዲሁም አባቴ ካህን ስለነበሩ ወደ ትምህርቱ እንድገባ አድርገውኛል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በስንት ዓመትዎ ነው አብነት ትምህርት የጀመሩት?**

**መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ፡-** ትምህርት የጀመርሁት በአራት ዓመቴ ነው፡፡ አባቴ ቀን እቤት ቁጭ ሲሉ፣ ማታም ለጸሎት ሲነሡ እየቀሰቀሱኝ ፊደል ያስቈጥሩኝ ነበር፡፡ ሌሊትም ቢሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ይዘውኝ እየሄዱ በመንፈሳዊ አገልግሎት እንድተጋ ያደርጉኝ ነበር፡፡ ስለዚህ እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ከብት እያገድሁ፣ በጎች እየጠበቅሁ፣ በተጓዳኝም የአብነት ትምህርቴን እየተማርሁ ነው ያደግሁት፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በቤት ፊደል መቍጠር የተጀመረው ትምህርት በመደበኛነት እንዴት እያደገ ሔደ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** አባቴ ከአካባቢያችን ትንሽ ራቅ ብሎ በሚገኘው ደብረ ጽጌ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ያገለግሉ ነበር፡፡ ቄሰ ገበዝ ስለሆኑ ዘወትር ይዘውኝ ይሄዱ ጀመር፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ ስመ ጥር አባቶች ስለነበሩ የአብነት ትምህርቱም በዚያው ይሰጥ ነበር፡፡ ከሚያስተምሩት መምህራን መካከል ደግሞ አባቴ አንደኛው ናቸው፡፡ የአቋቋም፣ የቅኔ፣ የመጻሕፍት መምህራን ባይኖሩም እስከ ግብረ ዲቁናና ቅስና ድረስ ያለው ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ እኔም አባቴን ጨምሮ እዚያው ካሉ መምህራን ዘንድ ዳዊትን፣ ውዳሴ ማርያምንና ዜማ ተምሬአለሁ፡፡ ለግብረ ዲቁና የሚያበቃኝን ትምህርት እንደጨረስኩ በ፲፱፻፸፩ ዓ.ም ታኅሣሥ ፫ ቀን ዲቁና ተቀበልሁ፡፡ በጊዜው በነበረው ጥንታዊ ልማድ መሠረትም አባቴ ግብር አዘጋጅተው፣ ወዳጅ ዘመዱን፣ የአካባቢውን ምእመናን፣ ካህናት አባቶችን ጠሩ፡፡ ሁሉም "የገ/ሥላሴ ልጅ ዲቁና ተቀብሏል፤ ምሥጢርም አይቷል፤ ሁላችሁም እንዳትቀሩ፤" እያሉ ተሰባሰቡ፤ ድግሱ ተበላ፤ ተጠጣ፤ በመጨረሻም ካህናትና ሽማግሌዎች ሁሉም ትልቅ ቦታ እንድደርስ መረቁኝ፡፡ ከዚህም በኋላ ዲቁና በተቀበልሁ በወሩ ጥር ፩ ቀን መቀደስ ጀመርሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ከዲቁና ትምህርት በኋላ በአገልግሎቱ ነው የቀጠሉት ወይስ በአብነት ትምህርቱ የዘለቁት?**

**መምህር ኀሩይ፡-** ዲቁናን ከተቀበልሁ በኋላ ወደ አገልግሎቱ ብቻ አላተኮርሁም፡፡ በእርግጥ ዲቁናን ስቀበል የሰዓታት ትምህርትን አጋምሼ ነበር፡፡ አባቴም በመንፈሳዊ ትምህርት እንድቀጥል ስለሚፈልጉ በአገልግሎቱ ብቻ ሳይሆን በትምህርቱም እንድገፋ ያበረታቱኝ ነበር፡፡ በተጨማሪም በቤት ውስጥም ይሁን ከቤት ውጪ ባለው ሥራ ብዙም እንድሠራ አይፈልጉም፡፡ ከሁሉም በተለየ መልኩ ትምህርት ላይ እንዳተኩር ይጥሩ ነበር፡፡ "አንተ ብቻ ተማር" ነበር የሚሉኝ፡፡ እኔም ትኩረቴን በትምህርት ላይ አደረግሁ፡፡ ከዲቁና በኋላ ቀጥዬ የተማርሁት ቅኔ ነው፡፡ አዲግራት ደብረ መዓር የሚባል ቦታ የኔታ ንጉሤ ዘንድ በስድስት ወር ውስጥ ቅኔን ተቀኘሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ሐውዜን ከተማ በማቅናት የኔታ ሐረገ ወይን ዘንድ ያጋመስሁትን የሰዓታት ትምህርትና የውዳሴ ማርያም ዜማን አጠናቀቅሁ፡፡ እርሳቸው ጋር ለሁለት ዓመት ያህል እንደቆየሁ ቀደም ብዬ የተማርሁት ቅኔን በደንብ ለማስፋፋት ወደ ዐድዋ አቀናሁ፡፡ በዐድዋ ከተማ ልዩ ስሙ ኮከፋ በሚባል አካባቢ ከየኔታ ፍስሓ ዘንድ ቅኔን እንደገና ተማርሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ቅኔን በድጋሜ ለመማር የወሰኑት ቅኔ ምን ያህል ቢስብዎ ነው?**

**መምህር ኀሩይ፡-** በመጀመሪያ የመራኝ እግዚአብሔር ነው፡፡ ቅኔ ደግሞ በባሕርዩ አዲስ ድርሰት ነው፡፡ አዲስ ድርሰት እንደመሆኑ መጠን የመጻሕፍትን መንገድ የሚገልጽ ብርሃን ነው፡፡ ይህ ጠባዩ ሁሌም ይስበኛል፡፡ በተጨማሪ የክብረ በዓላትና የንግሥ ቀናት ላይ ቅኔ ተቀኙ ስለሚባል ያን ጊዜ እንዳላፍር ብዬ ነው በሁለተኛ ደረጃ ተመልሼ ቅኔን የተማርሁት፡፡ ቀደም ብዬ ቅኔን በመማሬ ብዙ ጠቅሞኛል፣ የመጻሕፍትን ምሥጢር እንድመረምርና በጥልቀት እንድረዳ አግዞኛል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ከዚያ በኋላ ወዴት አመሩ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** ከቅኔ በኋላ በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ወደ መቐሌ አቅንቼ አቡነ ዮሐንስ ቀዳማዊ በመሠረቱት በደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከየኔታ መንግሥቱ ዘንድ ተቀምጬ ለሁለት ዓመታት ዜማ፣ ምዕራፍና ጾመ ድጓን ተማርኩ፡፡ ከዚያ በኋላ በ፲፱፻፹፩ ዓ.ም አቋቋምን ለመማር ወደ ጎንደር ዘለቅሁ፡፡ በጎንደር ደብረ ምጥማቅ በሚባል ቦታ ከየኔታ ጽጌ፣

ፊት ሚካኤል በሚባል አካባቢ ደግሞ ከየኔታ ኤልያስ ለሰባት ዓመታት አቋቋምን ተማርሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ከዚያስ የትኛውን የአብነት ትምህርት ተማሩ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** ከዚያ በኋላ ያለውን የአብነት ትምህርት የቀጠልኩት በአዲስ አበባ ነው። ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በመሪጌትነት እያገለገልሁ ባለኝ ትርፍ ሰዓት በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከየኔታ ተክሌ ቅዳሴ መማር ጀመርሁ። ከእርሳቸው ዘንድ ለሰባት ዓመታት እንደተማርሁኝ በ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ወደ ደብረ ዓባይ በመሄድ ለስድስት ወራት ያህል ቀንም ሌትም እያጠናሁ ቅዳሴ አስመስክሬ ወደ ደብሬ ተመልሼ መጣሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በልጅነት የትምህርት ዘመንዎ የትኛው ትምህርት ለእርስዎ ፈታኝና አስቸጋሪ ነበር?**

**መምህር ኀሩይ፡-** ትምህርት የጀመርሁት በቤት ውስጥ ስለሆነ ተፈትኜበታለሁ የምለው ብዙም የለም። ነገር ግን አቦጊዳ (አ በ ገ ደ) ትንሽ ይከብደኝ ነበር። በኋላ መጻሕፍትን ማንበብ ስጀምር በደንብ ለመድሁት። አንዳንድ ደግሞ አባቴ ቀን ያስተማሩኝ ማታ ላይ ድገመው ይሉኛል። የልጅነት ባሕርይ ሆኖ እኔ ወደ ጨዋታ ስለማደላ አልደገመውም ነበር። እርሳቸው ሲመጡ ወይም ከጎኔ ሲሆኑ ብቻ ነበር የምደግመው። በተለይ ደግሞ እኛ ቤት አንድ ልማድ ነበር። ሳምንቱን ሙሉ የተማርነውን የምንፈተንበት ቀናት ነበሩን፤ እነዚህ ቀናት ቅዳሜና እሑድ ናቸው። አባቴ ሳምንቱን ሙሉ ያስተማሩኝን በእነዚህ ቀናት ይፈትኑኛል። ያን ጊዜ መድገም ያቅተኛል፤ ምክንያቱም ጨዋታ እየሳበኝ ተከታትዬ ስለማላጠና ያስቸግረኝ ነበር። በዚህ ጊዜ አባቴም ይገሥጹኛል፣ ይቈጡኛል። በእሳቸው ጥረትና ክትትል በደንብ ትምህርቴን እንዳጠና፣ ለዚህ ደረጃና መዓርግ እንድደርስ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ አግዘውኛል። አባቴ የአቡነ ዐቢየ እግዚእ ቤተ ክርስቲያንን ተክለው አሁንም ድረስ እያስተማሩ ይገኛሉ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ከትምህርት በኋላ ወደ አገልግሎት እንዴት ገቡ? የትስ ማገልገል ጀመሩ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** አቋቋምን ከተማርሁ በኋላ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከመምህሬ የኔታ ኤልያስ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። አዲስ አበባ እንደመጣሁ አራት ኪሎ በሚገኘው በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ደጅ ጥናት ያዝሁኝ። ለስምንት ወራት ደጅ ከጠናሁ በኋላ እዚያ መቀጠሉ ስላልተሳካ በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ወደ መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በመሪጌትነትና በሰዓታት ቋሚነት ተቀጥሬ መጣሁ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በዚሁ ቤተ ክርስቲያን እያገለገልሁ እገኛለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን በአሁኑ ሰዓት በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ያለዎት የአገልግሎት ድርሻ ምንድን ነው? ከመደበኛ አገልግሎትዎ ውጭ የሚሳተፉባቸው አገልግሎቶችስ ይኖራሉ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቅዳሴ መምህር በመሆን አገለግላለሁ። ከቅዳሴ መምህርነት በተጨማሪም በሌሎች አገልግሎቶችም እሳተፋለሁ። በማኅሌት፣ ሰዓታት በመቆም፣ ሰሞነኛ በምሆንበት ጊዜ ደግሞ ፍትሐት እፈታለሁ። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዐት የእኔ ነው፣ የእከሌ ነው የሚባል ነገር ስለሌለ የተገኘውን በምችለው ዐቅም እሠራለሁ። በመደበኛነት ግን በቅዳሴ መምህርነት እያገለገልሁ እገኛለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ወንበር ዘርግተው ማስተማር የጀመሩት መቼ ነው? ምህ ያህል ተማሪዎች ይዘው ማስተማር ጀመሩ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** በመሪጌትነት ተቀጥሬ ባገለግልም ብዙ ጊዜ መንፈሴ ወደ ማስተማሩ ነበር የሚሳበው። በልጅነቴ ሕፃናትን ሰብስቤ ከቤታችን በራፍ ላይ አስተምራቸው ነበር። እነርሱም እኔን ከበውኝ ፊደል ይቈጥሩ ነበር። የዜማ መምህሬ የኔታ መንግሥቱ መቐሌ እንድቀር አጥብቀው ይፈልጉ ስለነበር "እሱ የተፈጠረው ለመምህርነት ነው ድጓ ብቻ ይማር" ይሉ ነበር። እግዚአብሔር አልፈቀደምና ትምህርቴን እንደጨረስሁ መቐሌን ትቼ ወደ ጎንደር አቀናሁ። ጎንደርም እያለሁ አቋቋም ለማስመስከር አስብ ነበር፤ አልተሳካም። ነገር ግን መምህርነት እንዳይቀርብኝ ስለፈለገ ወደዚህ ወደ ቅዳሴ መምህርነት አምጥቶ እዚህ አድርሶኛል። እኔ ዐቅምና ችሎታ ኖሮኝ ሳይሆን እርሱ ፈቅዶ ነው ወደዚህ የመራኝ። ሆኖም ግን በዋናነት ወንበር ዘርግቼ ማስተማር የጀመርሁት ደብረ ዓባይ ሄጄ ካስመሰከርኩ በኋላ በዚሁ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መጠለያ ሰኔ ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ነው። በመጠለያ ውስጥ ወንበር ዘርግቼ ማስተማር ስጀምር የቤተ ክርስቲያኑ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ አባቶችም ተማሪዎቼ ነበሩና በትንሹ ቍጥራቸው ከ፲ በላይ ነበር።

# “ንስሓ አባት የሰላም አዋጅ ነጋሪ፤ ኃጢአትን የሚያክም መንፈሳዊ ሐኪምም ነው”

***ክፍል ሁለት***



**ቀሲስ ይግዛው መኮንን**

*በካሣሁን ለምለሙ*

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትማችን ደግሞ ክፍል ሁለትን ይዘንላችሁ ቀርበናል። በጥሞና ትከታተሉ ዘንድ ግብዣችን ነው።***

**ስምዐ ጽድቅ፡- አንድ ሰው ንስሓ አባት ለመሆን ምን ዓይነት ቅድመ ዝግጅት ያስፈልገዋል? ምእመናንስ ንስሓ አባት ለመያዝ ምን ማድረግ አለባቸው?**

**ቀሲስ ይግዛው፡-** የንስሓ አባት ለመሆን ካህን መሆን የመጀመሪያው መሥፈርት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ራስን መግዛትና ቤትን መምራት መቻል ደግሞ ወሳኝ ቅድመ ዝግጅቶች ናቸው። ቤትን መምራት ስንል ልጆቹንና ባለቤቱን በትክክል መምራትና ማስተዳደር የሚችል ማለታችን ነው። ቤተሰቡን መምራትና ማስተዳደር የማይችል ካህን (አባት) ሌሎችን መምራት ማስተዳደር አይችልም። ካህን ራሱን የገዛ፣ የመራ፣ ቁጥብ፣ አልባሌ ቦታ የማይገኝና ሰብእናው ለሥጋ ልጆቹም ሆነ ለንስሓ ልጆቹ አርአያ መሆን የሚችል መሆን አለበት። ካህኑ የማይቈርብና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ ከሆነ ልጆቹን “ቊረቡ በቤቱ ተመላለሱ” ብሎ ለማዘዝም ሆነ ለመምከር ይከብደዋል። ልጆቹን ጹሙ ብሎ እርሱ የማይጾም ከሆነ፤ አልባሌ ቦታ አትገኙ ብሎ እርሱ አልባሌ ቦታ የሚገኝ ከሆነ ከአባትነት ደረጃ መውረድ ይመጣል። አባቶች ካህናት በንጽሕናቸው፤ በቅድስናታቸውና በአርአያነታቸው እጅግ የተመሰከረላቸውና የተከበሩ ሊሆኑ ይገባል።

ካህናት ሌላ አካልን ከመምራታቸው ከማስተማራቸውም በፊት መማርና በዕውቀት የበለጸጉ ሊሆኑ ይገባል። የአብነት ትምህርትን ከዘመናዊው ትምህርት ጋር አቀናጅተው በመማር በሁለት ጎን የተሳሉ ሰይፎች መሆን አለባቸው። ምክንያቱም ከማስተማር መማር ስለሚቀድም ነው። የዘመኑን ትውልድ በዕውቀት መቅደም ካልሆነም ደግሞ መከተል ብልህነት ነው። አባቶቻችን የተሳካ አገልግሎት እንዲፈጽሙ የትውልዱን ሥነ ልቡና መረዳት አለባቸው። ትውልዱን በቆየው መንፈሳዊ ዘዴ ለመምራት መሞከር ዋጋ ያስከፍላልና። የዛሬውና የትላንቱ ትውልድ አንድ ዓይነት እንዳልሆነ መረዳትም ተገቢ ነው። የዛሬው ትውልድ ከቀደመው ትውልድ የቀደመ ነው፤ የተማረ የተመራመረ ነው። ይህንን ትውልድ አባቶች ለማስተማር ሲፈልጉ ከትውልዱ ቀድመው ተምረውና ተሽለው መቅረብ ይጠበቅባዋል። በዓለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዕውቀት የተሻለ ነን መቅረባችን ትውልዱ በእውነተኛ መንገድ ለመቅረጽ ያግዘናል። ‹‹ከእኔ በላይ ያወቀ የተማረ ይኖራል›› ብሎ በማሰብ ትውልዱን ለማገልገል መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ትውልዱ ምን እንደሚፈልግና በምን ዓይነት መንገድ መቅረብ እንዳለብን ለመረዳት መንፈሳዊ አስተሳሰቦችን ገንዘብ ማድረግ ያስፈልጋል። በፍጹም ልብና በአገልጋይነት ስሜት ወስኖ ለማገልገል መነሣትም መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ይህም ሲባል ለማገልገል ቁርጠኛ መሆን ማለት ነው። ሰነፍ፣ ትጉህ፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ሀብታም፣ ድኃ፣ ወጣትና ልጅ ይኖራልና እነዚህን በተለያየ ዓይነት ሁኔታ የመጡ ምእመናንን በእኩል ዐይን ለማገልገል ቀና መሆን ያስፈልጋል። የተገልጋይን ሥነ ልቡና ካህኑ በደንብ መረዳትም አለበት። አንድ ካህን ንስሓ ልጆችን ሲቀበል ክርስትናቸውን ብቻ መሥፈርቱ ሊያደርግ ይገባል። የሰዎች ማንነት ክርስትና ነውና ንስሓ አባት

በልጆቹ ማኅበራዊ ኑሮ በሽምግልናም ሆነ በማስታረቅ ለመሳተፍ ቀርጦ የወሰነ አባት መሆን አለበት። በነዘን ጊዜ የሚያጽናና፣ሥጋዊ ፍላጎትን ብቻ ሽቶ መንፈሳዊ ፍላጎትን የሚተው መሆን የለበትም። ንስሓ አባት ልጆቹን መጥኖ መቀበል የሚችልና ለምን እንደተቀበላቸው የሚረዳ መሆን ይኖርበታል። ቤተ ክርስቲያናችን አንድ ሰው ንስሓ አባት ለመሆን የሚያበቃውን የተገደበ ደንብ ማዘጋጀት አለባት። ሕገ ደንብ ከማዘጋጀት በተጨማሪ ተፈጻሚነቱን መከታተል ያስፈልጋታል። አንድ ሰው ካህን ለመሆን ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅበት የተቀመጠ ሕግ ባይኖርም ንስሓ አባት ለመሆንም ሆነ ክህነት ለመቀበል መስከንና መብሰል ይጠበቅበታል። አንድ ያልበሰለና ያልሰከነ የሃያ ዓመት ወጣት ክህነት ቢቀበል ለመምከርም ሆነ ለማስተማር የሚቸገር ይሆናል። ስለዚህ ክህነት ለመቀበልና የንስሓ አባት ለመሆን ዕድሜ በራሱ ወሳኝነት አለው።

ምእመናንም መጀመሪያ ንስሓ አባት ለመያዝ ሲያስቡ ከራሳቸው ጋር ቀድመው መታረቅ አለባቸው። ይህም ማለት በሕገ እግዚአብሔር ለመመራት መወሰን ማለት ነው። ንስሓ አባት የሚለውን ለመስማት፣ ለመታዘዝና ለመፈጸም ወስነው መምጣት አለባቸው። ምእመናን ንስሓ አባት መያዝ ለምን እንደፈለጉ ጠንቅቀው ማወቅም አለባቸው። ጉዳይ ሲኖራቸው ብቻ ንስሓ አባት ለመያዝ ከመሯሯጥ ይልቅ ዕድሜ ለንስሓ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሰው ንስሓ አባት መያዝ አለበት። ንስሓ አባት መያዝ ለነፍስ ዋስትና ለማግኘትና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ስለሆነም ንስሓ አባት የሚያዘው ለተወሰኑ ቀናት መርሐ ግብራት ብቻ ታስቦ ሳይሆን ምእመኑ በሕይወት እስካለ ድረስ መሆን አለበት።

ምእመናን ንስሓ አባት ከያዙ በኋላ ለመታዘዝና ንስሓ ለመግባት መዘጋጀት፤ ሥጋ ወደሙን ለመቀበልና አሥራቱን ለማውጣት የወሰኑ መሆን አለባቸው። ምእመናን ንስሓ አባት ከመያዛቸው በፊት ማንን መያዝ እንዳለባቸው መወሰን ያስፈልጋቸዋል። በንስሓ አባትነት የሚያዟቸውን አባቶች በተቻለ መጠን ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው። በዚህ ዘመን የቁጥጥር ሥርዓት ስሌለ እውነተኛ አባት የሆነውና ያልሆነው ለመለየት ያስቸጋራል። ሁሉም እውነተኛ ካህን ሊመስል ይችላል፤ ምእመናን እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆኑ ካህናትን ከሌሎች መለየት አለባቸው። ካህኑ ለማስተማር፣ ለመናዘዝ፣ በማንኛውም ወይም አስፈላጊ በሆነ ማኅበራዊ ጉዳይ ላይ ለመገኘት ፈቃደኛ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን በትክክል የምታውቀው በሥርዓት የተሾመ አባት መሆኑን መገንዘብ ተገቢም ነው። በአጠቃላይ ምእመናን ንስሓ አባት ከመያዛቸው በፊት የካህኑን ምንነትና ማንነት በተገቢ መንገድ መለየት ይገባቸዋል።

**ስምዐ ጽድቅ፦ ከርስዎ ልምድና ተሞክሮ አንጻር በንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነት መካከል የሚስተዋሉ ችግሮች ምን ምን ናቸው? ችግሮቹንስ እንዴት ትፈታላችሁ?**

**ቀሲስ ይግዛው፦** የመጀመሪያው ችግር አለመረዳዳት ነው። ይህም የንስሓ አባት የንስሓ ልጅን አለመረዳት ወይም የንስሓ ልጅ የንስሓ አባትን አለመረዳት ማለት ነው። በዚህ መካከል አለመግባባት ይፈጠራል። በዚህ ምክንያት ትኩረት መነፋፈግ ይስተዋላል። በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት ለመፍታት በተለይ ካህኑ ተነሳሒው መጠየቅ ማወያየት ይጠበቅበታል። አባት ልጆቹን በቁጥር የተመጠኑ አድርጎ ያለመያዝና ክትትል ያለማድረግ ችግር ይስተዋላል። በእኔ ተሞክሮ እንደዚህ ዓይነት ችግሮችን አላስተናግድም። ልጆቼን መጥኜ እቀበላለሁ፤ ከዚያም ከልጆቼ ጋር በቅርበት እገናኛለሁ። አንዳንድ ጊዜ አባቶች ንስሓ ልጆቻቸውን ለይተው የማወቅ ችግርም ይስተዋላል። ይህ ችግር የሚስተዋለው ደግሞ ንስሓ ልጆችን አብዝቶ ከመያዝ ይመነጫል።

በአንዳንድ አባቶች መንፈሳዊ አገልግሎትን ወደ ሥጋዊ ፍላጎት የመቀየር አዝማሚያ እንዳላቸው እንመለከታለን። እንደዚህ የሚያደርጉ አባቶች በትክክል ቤተ ክርስቲያንን የማይወክሉ ከነፍሳቸው ይልቅ ለሥጋቸው ዋጋ የሚሰጡ ናቸው። ‹‹ይህንን ነገር አድርግልኝ፣ ካለደረክልኝ አሰናብትአለሁ›› የሚሉ እንዳሉም እንረዳለን። እነዚህ ካህናት ቤተ ክርስቲያንንም ሌሎች ካህናትንም የሚወክሉ አይደለም። ምእመናንም ይህንን በትክክል መረዳት አለባቸው። አንዳንድ አባቶች የንስሓ ልጆችን ለመቀበል መሥፈርት የሚያዘጋጁ እንዳሉ ይሰማል። ይህ መንፈሳዊ ዋጋን መሥፈርት ያደረገ ከሆነ መልካም ነው። ነገር ግን ከመንፈሳዊ አገልግሎት ይልቅ ሥጋዊ ድሎትን የሚያስቀድም መሥፈርት ከሆነ ግን ተቀባይነት የለውም። የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓትና ወግም አይደለም።

ሌላው በንስሓ አባትና ልጅ የሚስተዋለው ከገደብ ያለፈ ግንኙነት ነው። እንደምንረዳው የንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነት የተገደበና ከመንፈሳዊ አባትና ልጅነት ውጭ የሆነ ግንኙነት ሊሆን አይገባም። የመሪና የተመሪ ዓይነት ግንኙነት ብቻ ሊኖራቸው ይገባል። ግንኙነቱ ካልተገደበ ከልክ ካለፈ ሥጋዊ ወደሆነ ነገር፣ ወደ ፈዛዛ ይቀየራል። ስለዚህ ጥንቃቄ የተሞላበት ግንኙነት ሊኖር ይገባል። በሌላ መልኩ አንዳንድ ለሥጋቸው ያደሉ አባቶች ሥጋዊ ፍላጎታቸው እስካልተሟላላቸው ጊዜ ድረስ የንስሓ ልጆቻቸውን እስከማስቸገር የሚደርሱ አሉ።
የንስሓ አባት የንስሓ ልጁን ለንስሓ፣ ለቅዱስ ቊርባን እንዲበቃ ያለመጣር፣ ሥጋ ወደሙ እንዲቀበልና ንስሓ

እንዲገባ ያለ ማስተማር ችግሮች ይስተዋላሉ:: ይሁን እንጂ የአንድ ንስሓ አባት ኃላፊነት ልጆቹን ለቅዱስ ቍርባን ማብቃት፣ ከዚያም መንግሥተ ሰማያት እንዲወርሱ ማገዝ ነው:: ልጆች ከንስሓ አባታቸው የሚፈልጉትን ትምህርትና ተግሣፅ የማያገኙበት አጋጣሚዎች ይስተዋሉ:: ችግሮች በካህናት ብቻ የሚስተዋሉ ሳይሆን በንስሓ ልጆችም በኩልም ለመታዘዝ ያለመፍቀድ፣ ንስሓ ለመቀበል ያለመዘጋጀት፣ በሥጋ ወደሙ ለመታተም ፍላጎት ያለማሳየትና ከክፉ መንገድ ለመመለስ መቸገር ይጠቀሳሉ::

በንስሓ አባትና ልጅ መካከል አልፎ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ለማረም መጀመሪያ ንስሓ አባቶች የእውነት መንፈሳዊ አባት ሆነው መገኘት አለባቸው:: ንስሓ አባቶች የእግዚአብሔር ተወካዮች ነን፤ "ተናገር በከንፈሬ ተቀመጥ በወንበሬ›› ተብለናል በማለት ራሳቸውን ከማንኛውም መጥፎ ነገር ሊጠብቁ ይገባል:: ራሳቸውን የጠበቁ ካህናት በልጆቻቸው ዘንድ ይከበራሉ:: ቁጥብ መሆን፤ ንስሓ አባቶች የልጆቻቸውን የንስሓ ምሥጢር መጠበቃቸው በመካከላቸው ያለውን መራራቅ ሊያጠበው ይችላል:: አባቶች መናዘዝ፤ ማስታረቅና ማስተማር ይጠበቅባቸዋል:: ንስሓ ልጆችም የታዛዥነት መንፈስ አዳብረው አባቶቻቸው የሚያዟቸውን ሁሉ በቅንነትና በታማኝነት መፈጸም ይኖርባቸዋል::

**ስምዐ ጽድቅ፡-** ንስሓ አባት ያላቸው ምእመናን ከሌላቸው ምእመናን ጋር ሲነጻጸሩ በተለየ ሁኔታ የሚያሳዩት የባሕርይ ለውጥ ምንድን ነው?

**ቀሲስ ይግዛው፡-** ሰው ፈሪሀ እግዚአብሔር የሚኖረው፣ ሃይማኖትን ከሥነ ምግባር ጋር አስተባብሮ መያዝ የሚችለው፣ ንስሓ ገብቶ ሥጋ ወደሙ መቀበል የሚፈቅደው የንስሓ አባት ሲኖረው ነው:: ሰው ንስሓ አባት ሲኖረው በሃይማኖት የጠነከረ የበረታ ይሆናል:: መልካም አሳቢ ጥሩ ተናጋሪ የመሆን ዕድሉም ሰፊ ነው:: ለሰውና ለእግዚአብሔር የተመቸና የቀረበ ይሆናል:: በአንጻሩ ሕይወቱን በመምህረ ንስሓ ያልመራ ሰው መልካም ፍሬ ሊያፈራባቸው የሚችልባቸውን ነገሮች ሁሉ ያጣል:: ንስሓ አባቶች የነፍስም የሥጋም አማካሪዎች በመሆናቸው ሕይወቱን በንስሓ አባት የማይመራ ሰው ከነፍስና ከሥጋ መግቦት ውጭ ይሆናል::

ንስሓ አባት ያለው ሰው ከችግር ወደ መፍትሔ ሲመጣ የሌለው ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወቱ ውሉን ያጣበትና ከኃጢአት ድጥ ወደ ማጥ እየገባ ሁልጊዜም በኃጢአት አረንቋ ውስጥ ይኖራል:: ንስሓ አባት ያለው በጸሎት ይታሰባል፤ ንስሓ አባት ያለው መንፈሳዊ ሕይወቱን በንስሓ አባቱ ይመራል፤ የሌለው ደግሞ በራሱ ይመራል:: በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ በራስ መመራት ደግሞ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል:: እንኳን ምእመናን ካህናትም ሳይቀር በንስሓ አባት መመራት አለባቸው:: በስሕተት ወደ ጨለማ የተጓዘ ሰው በንስሓ አባቱ አማካይነት በብርሃን ይመለሳል:: ምእመናን ንስሓ አባት ሲኖራቸው ትምህርተ ወንጌልን ያገኛሉ፤ ልጆቻቸውንም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያሳድጋሉ::

**ስምዐ ጽድቅ፡- አንዳንድ አካላት ከቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ ምእመናንን በንስሓ አባትነት የሚያገለግሉ አሉና፣ ለእነዚህ አካላት ምን መልእክት ያስተላልፋሉ?**

**ቀሲስ ይግዛው፡-** የክህነት አገልግሎትን በሚገባ ከተጠቀምንበት ሰማያዊ ዋጋ የሚያስገኝ ነው:: የአገልግሎታችን ዋጋ ብዙ በመሆኑ እግዚአብሔር በሰጠን ሥልጣነ ክህነት ምእመናንን በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል ይጠበቅብናል:: በደንብ መሥራት በደንብ መልፋት ያስፈልጋል:: ካህናት የተሾሙበትን ዓላማ በደንብ ከተረዱ ሁሉንም በእኩል ዐይንና በቅንነት ያገለግላሉ:: ካህናት በእግዚአብሔር የተሾሙት ምእመናንን በታማኝነትና በቅንነት እንዲያገለግሉ ነው::

እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ብቻ ማገልገል አስፈላጊ ነው:: ሥጋዊ ነገሮቻችንን ስናሳድድ መንፈሳዊ ነገሮችን እንዳናጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር እንደየድካማችን እንደሚዳኘን ሁሉ እኛም የሰው ልጆችን እንደየድካማቸው መዳኘት አለብን:: ግዴታን በተገቢ ሁኔታ መወጣት እንደሚያስፈልግም ያለመወጣት ደግሞ እንደሚያስጠይቅ መረዳት ተገቢ ነው:: አገልግሎትን ሰውን ከመረዳትና ከመርዳት መጀመር መልካም ነው:: ተምሮ የማያስተምር አገልግሎ እንደማይሰጥ እንደ ሰባራ ዕቃ ይቆጠራልና የተማረውን ለንስሓ ልጆቹ (ለተማሪዎቹ) ያለምንም ገደብ ማስተማር የጠበቅበታል:: ስለሆነም የንስሓ አባቶች በተሰጣቸው ጸጋ ልክ ማገልገል ይገባቸዋል::

**ስምዐ ጽድቅ፡- ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**ቀሲስ ይግዛው፡-** ንስሓ አባቶች በተገቢ መንገድ የአባትነታቸውን ድርሻ ይወጡ፤ የንስሓ ልጆችም የልጅነት ድርሻቸውን መወጣት አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያን ድርሻዋን ትወጣ ምእመናንም እንደዛው ድርሻቸውን ይወጡ:: አባቶች ንስሓ ልጆቻቸውን በደንብ ማወቅ አለባቸው:: ልጆችም አባቶቻቸውን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል:: መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን ሥራ ለመሥራት ተቀራርቦና ተመካክሮ መሥራት አስፈላጊ ነው እላለሁ::

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ለነበርን ቆይታ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን::**

**ቀሲስ ይግዛው፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ተአምረኛዋ የሾላ ዛፍ፤

በምኒልክ ብርሃኑ



ሰላም ለእናንተ ይሁን ልጆች! እንደምን አላችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን! በጣም ደኅና ነን፡፡ ልጆች! ትምህርት እንዴት ነው? በደንብ እየተከታተላችሁ ነው? ጎበዞች! ትምህርታችሁን በትኩረት መከታተል፣ የሚሰጣችሁን የቤት ሥራ በቶሎ መሥራት አለባችሁ፡፡ እንዲህ ካደረጋችሁ ጎበዝ ተማሪ መሆን ትችላላችሁ፡፡ ልጆች! በዛሬ ቆይታችን የምንማረው፣ እናታችን ድንግል ማርያም በግብፅ በረሃ ሳለች ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሆና በአንዲት የሾላ ዛፍ ላይ ያደረገችውን ተአምር ነው፡፡

ከዕለታት ባንድ ቀን እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጠባቂዋ ዮሴፍና ሰሎሜ ጋር ሆና በግብፅ በረሃ እየሔደች ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ በሚያቃጥለው በረሃ ሲሔዱ ሲሔዱ ደብረ ምጥማቅ ከምትባል ቦታ ደረሱ፡፡ በዚያም ቦታ ሳሉ ወንበዴዎች መጡባቸው፡፡ ወንበዴዎቹ ደግሞ የሰውን ንብረት የሚዘርፉ፣ የሚቀሙና የሚገድሉ ነበሩ፡፡ ድንግል ማርያምም እነርሱን በተመለከተቻቸው ጊዜ ‹ልጄን ይገድሉብኛል› ብላ በጣም ፈራች፡፡ ‹‹ወይኔ ከአገሬ የወጣሁት፤ በሩጫ የደከምሁት፣ በረሃ ለበረሃ የተንከራተትሁት ልጄን ከገዳዮች ላላድነው ነውን?›› እያለች ታለቅስ ነበር፡፡ ወንበዴዎቹ ግን ወደ እነርሱ መገሥገሣቸውን አላቆሙም፡፡

በዚህ ጊዜ ድንግል ማርያም ልጇን አዝላ ከወንበዴዎቹ የምትደበቅበትን ቦታ ትፈልግ ጀመር፡፡ ልጆች! በበረሃ ምንም መደበቂያ የለም…፤ ወንበዴዎቹ ደግሞ በፍጥነት እየቀረቧቸው ነው… እመቤታችን እጅግ ፈራች፤ ልቧም በጣም ተጨነቀ፤ ከዛም መደበቂያ ስትፈልግ…. ስትፈልግ…. አንዲት የሾላ ዛፍ አገኘች፡፡ እመቤታችንም በሾላ ዛፍ መደበቂያ ለማግኘት ሁለት ሦስት ጊዜ ዞረቻት፡፡ ነገር ግን ለእነርሱ የሚሆን ምንም መደበቂያ አላገኘችም፡፡

የምትደበቅበት ቦታ ባጣች ጊዜ የተወደደ ልጇን የኢየሱስ ክርስቶስን ቀኝ እጅ ይዛ እንዲህ አለቻት፡- ‹‹አንቺ የሾላ ዛፍ! አንቺ የሾላ ዛፍ! እስከምፈልገው ድረስ ፈጥነሽ ተከፈቺ›› ብላ በመስቀል አምሳል አማተበች፡፡ በዚህን ጊዜ አንድ ድንቅ ተአምር ሆነ፤ ያቺ ድፍን፣ ምንም መደበቂያ የሌላት የሾላ ዛፍ እንደቤት ሆና ተከፈተች፡፡

አይገርምም ልጆች! ምንም መደበቂያ ያልነበራት የሾላ ዛፍ በእመቤታችን ድንቅ ተአምር ስትከፈት!! ከዛም የሾላዋ ዛፍ እመቤታችንም፣ ሕፃኑ ኢየሱስም፣ ዮሴፍና ሰሎሜም፣ አህያዋንም ሁሉንም ደበቀቻቸው፡፡ ልክ እነርሱ ሲገቡ ዛፏ እንደቀድሞዋ ተመልሳ ገጠመች፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሲከተሏቸው የነበሩት ወንበዴዎች የሾላዋ ዛፍ አካባቢ ደረሱ፡፡ ነገር ግን አላገኙዋቸውም፡፡ ምክንያቱም ያቺ የሾላ ዛፍ ደብቃቸዋለች፡፡

ያን ጊዜም የሽፍቶቹ አለቃ ‹‹ሕፃኑን እና እናቱን አሁን በሾላው ዛፍ አጠገብ

ቆመው አይተናቸው አልነበር እንዴ? ወዴት ተሠወሩ?›› አያለ በቍጣና በንዴት ተናገረ። ሌሎቹም ወንበዴዎች ‹‹ወዴት ሄዱ? አሁን እኮ አይተናቸው ነበር!? ወደ ሰማይ ዐረጉ ወይንስ ወዴት ተደበቁ?›› እየተባባሉ እርስ በርስ ተጠያየቁ። የተደበቁበትን ቦታ ለማግኘት የሾላውን ዛፍ ይዞሩት ጀመር፤ ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም። ልጆች! እናንተ ግን የት እንደተደበቁ ታውቃላችሁ አይደል? ጎበዞች!

**አይገርምም ልጆች! ምንም መደበቂያ ያልነበራት የሾላ ዛፍ በእመቤታችን ድንቅ ተአምር ስትከፈት!! ከዛም የሾላዋ ዛፍ እመቤታችንም፣ ሕፃኑ ኢየሱስም፣ ዮሴፍና ሰሎሜም፣ አህያዋንም ሁሉንም ደበቀቻቸው። ልክ እነርሱ ሲገቡ ዛፏ እንደቀድሞዋ ተመልሳ ገጠመች።**

ወንበዴዎቹ የተደበቁበትን ቦታ በፍጹም ሊያውቁት አልቻሉም። ታዲያ በዚህ ጊዜ በሾላዋ ዛፍ ውስጥ የተደበቀችው አህያዋ ጮኸች። እነዚያም ወንበዴዎች ጩኸቱን በሰሙ ጊዜ፤ ‹‹ይህ ጩኸት ከየት ነው የመጣው?›› ብለው እርስ በእርስ ተጠያየቁ። ጩኸቱም ከሾላዋ ዛፍ ውስጥ እንደሆነ ባወቁ ጊዜ እጅግ ተደነቁ። ‹‹እንዴት በሾላዋ ዛፍ ውስጥ አህያዋ ልትጮህ ቻለች! እንዴትስ በውስጧ ገብተው ሊደበቁ ቻሉ!›› ብለው ተገረሙ። ሁሉም ወንበዴዎች በሾላዋ ዛፍ ውስጥ ገብተው መደበቃቸውን ባወቁ ጊዜ በጣም ተገረሙ። የሽፍቶቹም አለቃ ‹‹እነዚህ ጻድቆች የእግዚአብሔር ሰዎች ስለሆኑ ነው እንጂ ካለበለዚያማ እንዲህ ዐይነት ድንቅ ተአምር ለማንስ ይቻለዋል!›› አለ። ሌሎቹም በእነርሱ ላይ አደጋ ለማድረስ በማሰባቸው ተጸጽተው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ መጡበት ሄዱ።

እመቤታችንም ወንበዴዎቹ እንደሄዱ ባወቀች ጊዜ የተደበቁባት የሾላ ዛፍ ከውስጧ ይወጡ ዘንድ ‹‹አንቺ የሾላ ዛፍ! አንቺ የሾላ ዛፍ ተከፈቺ!›› አለቻት። ተአምረኛዋም የሾላ ዛፍ እንደበፊቱ ተከፈተች፤ እነርሱም ከውስጧ ወጡ። ከወጡም በኋላ ዛፏም እንደቀድሞዋ ገጠመች። በመጨረሻም ከብዙ ድካምና ጉዞ በኋላ ወደ አገራቸው በሰላም ተመለሱ።

ልጆች! እመቤታችን ያደረገችውን ተአምር ድንቅ ነው አይደል! በሉ ልጆች ለዛሬ በዚህ ይብቃን፤ በሚቀጥለው በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ። የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር።***

ምንጭ፡- (ተአምረ ማርያም። ተስፋ ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.፣ ፴፫ኛ ተአምር፣ ከገጽ ፻፴፬-፻፴፫)

# ፀጥታ ይከበር!

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

የእግዚአብሔር ቤት እጅግ የተቀደሰ፣ የተከበረ ቦታ ነው:: በዚያ ያለው ሁሉ ቅዱስ ነው:: የሚሠራውም ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የተቀደሰ ነው::

የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው:: ‹‹ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላልና›› (ኢሳ ፶፮፥ ፯)፣ ‹‹ ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል ተብሎ ተጽፏል እናንተ ግን የሌባና የቀማኛ ዋሻ አደረጋችኋት›› አላቸው:: ማቴ ፳፩፥፲፫) እንደተባለ:: በእግዚአብሔር ቤት የእግዚአብሔር መንፈስ ያድራል፤ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ይመላለሳሉ:: በእግዚአብሔር ቤት ትሑታን፣ ትጉሃን መንፈሳውያን ይመላለሳሉ:: ቦታው በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ መካከል ያለ መገናኛ ሥፍራ ነው:: አባታችን ያዕቆብ ‹‹ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራል፤ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህም የሰማይ ደጅ ነው:: (ዘፍ ፳፰፥ ፲፯) ብሎ ካደነቀው ራእዩን ካየባት ከቤቴል ክብር በእጅጉ በሚበልጥ ክብር የሚታይ፣ የሚታመን ሥፍራ ነው::

በዚያ ጸሎት፣ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ጸሎተ ሰዓታት፣ ማኅሌት፣ ጸሎተ ተክሊል፣ ጸሎተ ፍትሐት፣ ምሕላ፣ ሱባኤ፣ ትምህርት፣ ቡራኬ፣ ፈውስ፣ ራዕይ፣ ተአምራት ወዘተ … ሁሉ የሚደረግበት ታላቅ ሥፍራ ነው:: ከምንም በላይ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ሁሉ የሚከናወኑት በጸሎት ነው፤ በቤተ ክርቲስያን የተገኙ ሰዎች ሁሉ በዚያ ሥፍራ ተገኝተው መፈጸም ካለባቸው ነገር ሁሉ የመጀመሪያው ጸሎት ነው::

ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሥፍራ ነው:: የጸሎት ሥፍራ ደግሞ ፀጥታና ርጋታን ይፈልጋል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎትን ሲያስተምር ‹‹ጥቂት ፈቀቅ አለና በግንባሩ ሰግዶ ጸለየ::›› (ማቴ ፳፮፥ ፴፱) እንደተባለ ከደቀ መዛሙርቱ ራቅ ብሎ በጌቴሴማኒ አትክልት ሥፍራ መጸለዩን እናስታውሳለን:: ሰዎች ወደሌሉበትም ሥፍራ ሄዶ መጸለዩን እናስተውላለን ወንጌል ‹‹ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ::›› እንዳለ:: (ማር. ፩፥፴፭)

ቤተ ክርስቲያን በጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ አንጻር የጸሎት ቦታ ሆና የምታገለግል የተለየች ሥፍራ ናት:: ቤተ ክርስቲያን ፀጥታና ሰላም የሰፈነባት ጌታ በጸለየበት የቆሮንቶስ ምድረ በዳ አንጻር የተለየች የጸሎት፣ የስግደት ሥፍራ ናት:: ስለዚህ በዚያ የሚመላለሱ ወገኖች ሁሉ ፀጥታን የሚፈልጉ፣ ቤተ ክርስቲያን ፀጥታን የማስፈን ኃላፊነት ይጠበቅባታል::

ይህ ቦታ እግዚአብሔር የትሑታንን ጸሎት የሚቀበልበት የፀጥታ ሥፍራ ነው:: የእግዚአብሔር ዓይኖቹ በዚህ ቅዱስ ሥፍራ ናቸው:: ‹‹ባሪያህ ወደዚህ ሥፍራ የሚጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ፦ በዚያ ስሜ ይሆናል ወዳልኸው ሥፍራ ወደዚህ ቤት ዓይኖችህ ሌሊትና ቀን የተገለጡ ይሁኑ::››(፩ኛ ነገ ፰፥፳፱) ያለውን የጠቢቡን የጸሎት ቃል እናነባለን:: በዚህ ሥፍራ ደግሞ እግዚአብሔር በፀጥታ ውስጥ የብዙዎችን የልባቸውን የጸሎት ጩኸት ይሰማል:: የብዙዎችን የምስጋና ጩኸት ይሰማል:: እንዲህም ይላል ‹‹በፀሐይ ጮራ እንደ ደረቅ ትኩሳት፥ በአጨዳም ወራት እንደ ጠል ደመና ሆኜ በማደሪያዬ በፀጥታ ተቀምጬ እመለከታለሁ:: ›› (ኢሳ. ፲፰፥፬)

በእግዚአብሔር ቤት ብዙ ቅዱሳን በፀጥታ ሆነውይጸልያሉ፤ በከፍተኛ ተመስጦ ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኛሉ፤ ራእይን ያያሉ፤ ተአምራትንም ይሠራሉ፤ በብዙ ስግደት፣ ዕንባና ተማጽኖ ይማለላሉ:: ‹‹ወደ ኢየሩሳሌምም ከተመለሱ በኋላ በመቅደስ ስጸልይ ተመስጦ መጣብኝ፥›› (የሐዋ. ፳፪፥፲፯) ያለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ያስታውሰናል::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቃለ እግዚአብሔር የሚሰማባትም ድንቅ ሥፍራ ናት:: በዚች ሥፍራ ማገልገል የሚቻለው ፀጥታና ተመስጦ ሲኖር ብቻ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ በአገልግሎቱ ጊዜ ‹‹ጳውሎስ በደረጃው ላይ ቆሞ በእጁ ወደ ሕዝቡ ጠቀሰ፤ እጅግም ፀጥታ በሆነ ጊዜ በዕብራይስጥ ቋንቋ እየተናገረ እንዲህ አለ::…. (የሐዋ.ሥራ ፳፩፥፵) ይላል:: የቅዱሳንን ምክር ተግሣፅ በረከት ለማግኘት አስቀድሞ ፀጥታ መከበር አለበት::

ይቺ ሥፍራ ምእመናን የሚመላለሱባት፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጽምበት እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝባት፣ ምእመናንም በዚያ የሚሰበሰቡበትን መንፈሳዊ ዓላማ በተመስጦ ሆነው የሚፈጽሙባት የተቀደሰች ሥፍራ ናት:: ሥርዓቷም በእግዚአብሔር ፈቃድ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተሠራ ልዩ ሥርዓት ነው:: ጸጥታ ተመስጦን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን የምንሰማውን ነገር ማክብርን ያመለክታል:: በመቅድመ ተአምረ ማርያም ‹‹ወይኩን ዓቢይ አርምሞ ወአልቦ ዘይትናገር ፤ ፍጹም ዝምታ ይሁን የሚነጋገር አይኑር›› የሚለው ቃል የዚህ ማሳያ ነው::

በእግዚአብሔር ቤት የሚመላለስ ሁሉ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማክበር አለበት:: በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ባለን ቆይታ ሁሉ በውስጧ የሚፈጸሙ መንፈሳዊ ተግባራትን የማያውክ እንቅስቃሴ ሊኖረን ይገባል:: በቤቱ የሚኖረን የአገልግሎት፣ የጸሎትና የምስጋና ቆይታ ሁሉ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን በማያውክ የአገልግሎቱንም ሥርዓት በማይረብሽ መንገድ ማገልገልና መገልገል ይኖርብናል::

ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ቤት ለመገልገልና ለማገልገል ፀጥታ ዋንኛውና አስፈላጊው ጉዳይ ቢሆንም ዛሬ ዛሬ ፀጥታን በሚያደፈርስ፣ ከንቱ ድምፅ በሚፈጥር መንገድ ያለሥርዓት መንቀሳቀስ በአንዳንድ አጥቢያዎች እየተለመደ መጥቷል:: ይህ ሥርዓት የማጣት፣ ያለማወቅ፣ የመድፈር ነገር በጊዜው ካልታረመ ቅጣትን ያስከትላል::

ቤተ ክርስቲያን የሥርዓት ቤት እንደመሆኗ መጠን ሁሉም በሥርዓት መከናወን ሲገባው ሥርዓት እየተጣሰ፣ ሥርዓት አልበኝነት እየነገሠ ነው። እግዚአብሔር በሚመሰገንበት፣ ምእመናን ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት የቅዳሴ ሰዓት ከምእመናን እስከ ካህናት በወሬ ተጠምደው የግል ጉዳያቸውን ሲያወሩ ማየት እና መስማት የተለመደ ነው። በቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሥፍራ የሞቀ የደመቀ ወሬ የሚያካሂዱ፤ ከኢኮኖሚ እስከ ፖለቲካ፣ ከግብርና እስከ ንግድ ጉዳዮቻቸውን እያነሡ እየጣሉ የሚያወሩ ሰዎችን በቀላሉ መታዘብ ይቻላል። ቤተ እግዚአብሔርን ከንቱ የሆነ ዓላማዊ ወሬን ከምናወራባቸው የመዝናኛ ሥፍራዎች መለየት እንኳን የሚቸገሩ ብዙዎች ናቸው። በቅዳሴ ጊዜ የሚስቅ ካህን ቢኖር ቅጣቱ አንድ ሱባኤ ነው ሕዝባዊ ቢሆን በዚያው ጊዜ ይውጣ ስጋ ወደሙን አይቀበል ፍት.ነ አንቀጽ ፲፪ ቁጥር ፬፻፸፬።

ይህ ቅዳሴውን ከማወኩም በላይ የሰውን እይታ እና ሐሳብ የመስረቅ ኃይል አለው። ከሥርዓተ ቅዳሴው  ጅማሬ እስከ ፍጻሜው የሚታዩ ከሥርዓት የወጡ ትእይንቶች ከዚሁ ጋር የሚመደቡ ናቸው። ማንም ሰው በማይንቀሳቀስበት የቅዳሴ መጀመሪያ ላይ ሰዎች ወደ ውስጥ ለመግባት ሲሯሯጡ፣ ወንበር ከወዲያ ወዲህ ሲጎትቱ ማየት፣ ቅዳሴ ሳያልቅ መውጣት መግባት እንዲሁም አቋርጦ መሄድ የቤተ ክርስቲያንን ፀጥታ በእጅጉ እያወከ ነው። በሥርዓተ ቅዳሴ ምዕራፍ ሦስት ቁጥር አንድ ላይ ‹‹ጸሎተ ቅዳሴው ከተጀመረ በኋላ ዲያቆኑ (እትው በሰላም) እሾህ ሳይወጋችሁ እንቅፋት ሳይመታችሁ በሰላም ወደቤታችሁ ሂዱ ብሎ ሳያሰናብት ወጥቶ መሄድ አይገባም›› ይላልና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው ማንኛውም እንቅስቃሴ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል።

ከቤተ መቅደሱ ውጪ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያንም የሚታየው ተመሳሳይ እና የቤተ ክርስቲያንን አግልግሎት በእጅጉ የሚፈትን ነው። በተለይ በከተሞች ባሉ አጥቢያዎች አንዳንድ ሰዎች መኪናዎቻቸውን በግቢ ውስጥ አቁመው ‹‹አላርሞቻቸው›› የአጥቢያውን አገልግሎት ሲያውኩት ማየት እየተለመደ መጥቷል። ባለመኪናዎች ራሳቸውንም ሌሎችንም በማወክ ችግር ይፈጥራሉ። አንዳንድቹም  ከመቅደስ ተጠርተው የመኪና ‹‹አላርም›› የሚያጠፉ፣ ጸሎት አቋርጠው የመኪናዎቻቸው ጩኸት ለማጥፋት የሚሯሯጡ ሰዎችን ማየት እየተለመደ ነው።

አንዳንዶች በእጃቸው የያዙትን ስልካቸውን ድምፅ ለማጥፋት እየሰነፉ ስልካቸው በሚጠራ ጊዜ ዘፈንና ፉከራ በማሰማት የቤተ ክርስቲያንን ፀጥታ በእጅጉ ያውካሉ። ሌሎቹን በድምፅ ከማወክ አልፈው ጸሎት አቋርጠው ስልካቸውን አንሥተው ከንቱ ነገር (ሥጋዊ ጉዳይ) የሚያወሩ ወገኖችም አሉ። በስልካቸው የጀመሩትን ፀጥታ የማሳጣት ተግባር በራሳቸው የስልክ መልእክት ልውውጥ ይቀጥሉታል። በመልእክት ልውውጥ ከሚፈጥሩት ድምፅ አልፎ ደግሞ በሚያስተላልፉት መልእክት ይዘት የሰውን ጸሎት ልብ የሚበትኑ በርካቶች ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአገልጋዮች መካከል የሚፈጠር ንትርክ አላስፈላጊ ድምጽ ፀጥታን ያደፈርሳል። በየአጥቢያው ዙሪያ ያሉ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚፈጥሩት ሁከትም ሌላው ፀጥታን የሚነሣ አካሄድ ነው። ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ብዙም ሳንርቅ እዚያው በራፉ ላይ የምናየው የደራ ገበያ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት በእጅጉ የጎዳ፤ ከነውርነት አልፎ እንደ አንድ መልካም ነገር እየተቆጠረ ከመጣ ሰነባበተ። መንፈሳዊ ነገር ብቻ ሊታይባቸው የሚገቡ የቤተ ክርስቲያን ደጆች በምግብ እና በአልባሳት ተሞልተው ኢአማንያን እና አማንያን የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ሲገበያዩ በሚፈጥሩት ትርምስ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ሲታወክ አይቶና ሰምቶ ከመሄድ ባሻገር ቆም ብሎ ለምን? የሚል የለም።

በዓላት በሚከበሩባቸው የቤተ ክርስቲያን ቅጽሮች ዙሪያ አንዳንዴም የቤተ ክርስቲያንን ቅጽር ታከው ከተሠሩ ቤቶች ውስጥ የሚወጣው የጠጪዎች ሁካታ፣ የቡናና ሻይ ሽታ እና የብርጭቆዎች ካካታ የቤተ ክርስቲያንን የፀጥታ እና የጽሙና ቦታነት እየተፈታተነ ይገኛል። ከዐውደ ምሕረት የሚተላለፈውን ትምህርት ምእመናን መስማት እና መከታተል በማይችሉበት ደረጃ የሚረብሹ የነዳያን የልመና ድምጾች፣ ማዕተብ፣ የጸሎት መጻሕፍትና የመዝሙር ካሴት ለማሻሻጥ በሞንታርቦ የሚለቀቁ ድምጾች የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት በእጅጉ እየጎዱት ነው።

ይህ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዐት የመውጣት፣ የማፈንገጥ ፣ በዓለም ያለው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር የማስገባት አካሄድ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት ለማግኘትም ሆነ ለመስጠት ሥርዓት ያስፈልጋል። ጩኸት (ሁከት) በእግዚአብሔር ደጅ ማሰማት ፈጽሞ የማይገባ ነው። ሐዋርያው እንዳለው ‹‹እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም›› (፩ኛ ቆሮ. ፲፬፥፴፫)።

በእግዚአብሔር ቤት ሁሉም እንደ ፈለገ የሚያደርግበት አይደለም። ሥርዓት አለ። ‹‹ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።›› (፩ኛ ቆሮ. ፲፬፥፵) ተብሏልና። በቤተ ክርስቲያን ፀጥታን ማክበር የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አካል ነው። በመጽሐፈ ቅዳሴ (ሥርዓተ ቅዳሴ) ‹‹ክቡር ምሥጢርን ለመቀበል የተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ የእግዚአብሔርን ነገር ለመስማት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸጥታ ይቁሙ። የሚናገርም የሚስቅም አይኑር፤ ቤተክርስቲያን የነገር ቦታ አይደለችምና፤ የጸሎት ቦታ ነች እንጂ›› ተብሎ ተጽፏል። እንኳን በቤተ ክርስቲያን በቤታችንም የጸሎት ሥፍራችን ተመስጠን የሚሰጥ፣ ሐሳብን የሚሰበስብ የፀጥታ ቦታ መሆን አለበት። ይህን ማድረግ አስፈላጊ ነው። የጋራ የጸሎት ቤታችን የምሥጢራት ሁሉ መፈጸሚያ በሆነችው የቅድስናው ሥፍራ ደግሞ ፍጹም ፀጥታና ሰላም ያስፈልጋል።

ስለዚህ ፀጥታን የሚያደፈርስ የትኛውንም የማይገባ ተግባር ከመፈጸም መቆጠብ አለብን። ሐዋርያው ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ እንመክራችኋለን፤ ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤›› (፩ኛ ተሰ. ፭፥፲፬) በማለት እንደመከረን ሌሎችም ሲፈጽሙ በመምከር ከዚያም ሲያልፍ በመገሠፅ በእግዚአብሔር ቤት ሥርዓትን እናስከብር።

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር።***

# ከማኅበራዊ ሚዲያ ሱስ እንዴት ልላቀቅ?

**ክፍል ሁለት**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ ፦***

ሰዎች ነጋዴዎች ካልሆኑ በስተቀር ሁል ጊዜ ገበያ ሊሄዱ አይችሉም። ገበያ የሚሄዱት የሚገዙት ነገር ሲኖር፣ የሚገዙበትም ገንዘብ ሲኖራቸው፣ የሚገዙበት ጊዜ ሲኖር ነው። ሰዎች ሐኪም ካልሆኑ በስተቀር ሁልጊዜ ወደ ሆስፒታል ሊሄዱ አይችሉም። ታመው፣ የታመመ ለመጠየቅ፣ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ብቻ ነው። እንዲሁ ሰዎች ማኅበራዊ ሚዲያን ሊጠቀሙ የሚችሉበትን የሕይወታቸውን ምክንያት፣ የሚጠቀሙበትን ጊዜ፣ የሚጠቀሙበትን የመረጃ ማስተላለፊያ ምቹ ሁኔታ . . . ወዘተ በምክንያት መወሰን አለባቸው። ሁልጊዜም ከድረገጽ ጋር ቁርኝት ኖሮት ጊዜያትን በብዙ ሊያሳልፍ የሚችለው ከራሱ ከድረገጽ ጋር የተያያዘ ሙያዊ ምክንያት ያለው ሰው ብቻ ነው። እርሱም ቢሆን ሊሠራ በሚችልበት ውስን መስክ ላይ እንጂ ሁሉን ለመቃረም፣ የተዘራውን ሁሉ ለማጨድ የተበተነውን ሁሉ ለመሰብሰብ፣ የተሠራጨውን ሁሉ ለማየትና ለመስማት ሊሠማራ አይችልም።

ይህ ከታመነ ማኅበራዊ ሚዲያን አዘውትረን እንድንጠቀም ያስገደዱን ጫና የፈጠሩብን የተለዩ ምክንያቶች ካሉ እነዚያን በውል መመርምር ያስፈልጋል። ከብርቱ ኀዘን፣ ከብቸኝነት፣ ከሰዎች ፍቅር ማጣት እንዲሁም ከጭንቀት ወይም ከድብርት የተነሣ ወይም ሌላ ምክንያት ኖሮ ከእነዚህ ለማምለጥ የተጠቀምንበት መሸሸጊያ ሆኖም ከሆነ ራስን መመርመር ጠቃሚ ነው። የኑሮውና የአኗኗር ሁኔታው መለዋወጥ ሰዎች ከሰዎች እየራቁ በወከባ ውስጥ በቆዩ ቁጥር ግራ የተጋቡ ሰዎችን ያገኙና ከብቸኝነት የዳኑ እየመሰላቸው ብዙ ጊዜያትን ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በማየት እንደሚያሳልፉ ይታወቃልና።

በሌላ በኩል ደግሞ በማኅበራዊ ሚዲያ ከሚለቀቁ ነገሮች የሚገኝ የደስታ ስሜትም ከገደብ ባለፈ ደጋግመን የመጠቀም ፍላጎትን ይተክልብናል። ድራማዎችን፣ ዘፈኖችን፣ ቀልዶችን፣ የግለሰብ ገመናዎችን፣ የታዋቂ ሰዎችን ዝና... ሰዎች በማየትና በመስማት ያለገደብ ደስ ይሰኙበታል። ከዚህም ሲሻገር ወደከፋው ደንበር ይጠጉና የዝሙት ፊልሞችንና ሥዕሎችን፣ ቅስቀሳዎች በመከታተልም ሊጠመዱ ይችላሉ። ይህም የሚከታተላቸው ያጡ ሕፃናት በእጅጉ የሚጣፍጧቸውን ምግቦች ያለልክ በመወስዳቸው ሆዳቸው እንደሚታወክበት ያለ ችግር ያጋጥማቸዋል።

ስለዚህ ውድ ጠያቂያችንም ሆነ ሌሎች በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች የመጀመሪያ ርምጃቸው መሆን ያለበት ማኅበራዊ ሚዲያን የመጠቀም ዓላማን፣ የጊዜ መጠንን፣ ዓይነትን በውል ለይቶ መጠቀም ያስፈልጋል።

ብዙ ጊዜ ከምንሰናከልባቸው ምክንያቶች አንዱ ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ነገር በሚገባ ለይቶ አለማወቅ ወይም ያወቅትን ነገር ነገ ማድረግ እችላለሁ በማለት ዛሬን በከንቱ ወሬ፣ በማይጠቅም መዘናጋት ውስጥ በከንቱ ፍለጋ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ተጣብቆ በመዋል ዛሬ ማድረግ የሚገባኝን ነገር ከነገ ወዲያ አደርጋለሁ ብሎ መዘናጋት ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ሱስ ውስጥ ያለ ሰው ከንቱ ደስታውን የሚያገኘው ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ በመጣበቅ አድርጎ ስለያዘው ነገ የሚመጣውም ቀን የሱሱ እንጂ የእርሱ አይሆንምና ከንቱ መባከን ነው።

ይህ ግን መባከን ብቻም ሳይሆን መመካትም፣ ነገ በእግዚአብሔር የተያዘች ቀን መሆኗንም መዘንጋት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ‹‹ቀን የሚያመጣውን ምን እንደ ሆነ አታውቅምና ነገ በሚሆነው አትመካ›› ዳግመኛም ‹‹አሁንም፦ ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና›› ይላልና። (ምሳ.፳፯፥፩፣ ያዕ ፬፥ ፲፫-፲፬)

ከዚህ የዘለለ ችግር ያለባቸው ሰዎች ደግሞ ከነበሩበት ልማድ በሂደት ለመውጣት ልዩ ልዩ ርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው ‹‹ዓይንህ ብታሰናክል አውጥተህ ጣላት›› በተባለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት መመራት ነው(ማቴ.፭፥፳፱)። ማኅበራዊ ሚዲያ ሕይወታችንን ያባከነ ጨካኝ ገዢ ከሆነብን ከቤታችን ማጥፋት ያስፈልጋል። በእጅ ስልኮቻችን በየቦታው ሁሉ በመጠቀም፣ አለዚያም በቢሮአችን ውስጥ ባሉ ኮምፒውተሮች በመጠቀም የምንፈልገን ከሆነ ነገሩን ለመግታት ማቀጣጠያዎችን ከእሳቱ ማራቅ አስፈላጊ ነውና የምንፈልጋቸውን መተግበሪያዎች ብቻ አስቀርተን ሌሎችን ማጥፋት ይኖርብናል። ይህ እኛን ለሌላ አስፈላጊ ነገር ለማትጋት፣ ሱስን ደግሞ ለማሸነፍ ይበጃል።

በእዚህ ዓይነት ሱስ ለተያዙ ሰዎች ግን እነዚህን ርምጃዎች ብቻ በመውሰድ በቀላሉ ከልማዱ መራቅ አይቻል ይሆናል። የእጅ ስልኮቻችንን በመጠቀም በከንቱ እናሳልፈው የነበረውን

ጊዜ ጠቃሚና ትርጉም ባላቸው ተግባራት መተካት አለብን:: እነዚህን በመታከት መንፈስ ቸል ያልናቸውን የሕይወታችንን ቁልፍ ተግባራት በሚገባቸው ጊዜ ወደ መፈጸም መመለስ አለበን:: በጊዜያቸው ካልሠራናቸው በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም ሕይወታችን የለሾች ውጤት አልባዎች እንሆናለን:: ይህንንም አስመልክቶ መጽሐፍ ‹‹ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት::›› በማለት ይመክረናል::(ገላ. ፮፥ ፱)

ስሆነም የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችንን ከምንሠራቸው ጠቃሚ ተግባሮቻችን ጋር የተገናዘቡ አድርጎ በአዲስ ስልት መራመድ ያስፈልጋል:: በዕለት ዕለት ከምናከናውናቸው ጠቃሚ ጉዳዮቻችን በፊት በመግባት እጅግ ብዙ ጊዜያችንን ካባከንን፣ አእምሮአችንን ካደከምን በኋላ መመለስ ስለሚሆን ተግባሮቻችንን ውጤታማ ሆነን ልናከናውን አንችልም:: ቀድምን ማከናወናችን ብቻ ሳይሆን ከሕይወታችን ጋር ያልተገናዘበ አጠቃቀም ከሆነ ጉዳቱ ያው ነው::

መማር ወይም መሠልጠን፣ መነገድ፣ ማረስ፣ ልዩ ልዩ የዕደ ጥበብ ሥራዎች መሥራት ወዘተ . . . ጀምረን ከሆነ ብዙ ጊዜያችንን በእነዚህ የራሳችንንና የቤተሰባችንን ኑሮ በሚያሻሽሉ ተግባራት ላይ እያሳለፍን እነዚህን ተግባራት ሊደግፉ የሚችሉ የማኅበራዊ ሚዲያ መረጃዎችን ለማግኘት ልንጠቀም እንችላለን:: ሕይወታችንን በተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ጠምደን ከሆነ ለዚህ አገልግሎታችን በሚጠቅም መንገድ በጊዜ ገድበን ይዘት መርጠን በታላቅ ጥንቃቄ ማኅበራዊ ሚዲያን ልንጠቀም እንችላለን:: ጥንቃቄ የጎደለው ሕይወት ለጉዳት ያጋልጣል:: ‹‹ጥንቃቄ ይጠብቅሃል፥ ማስተዋልም ይጋርድሃል›› ያለውን የጠቢቡን ምክር መከተል ያስፈልጋል:: (ምሳ. ፪፥ ፲፩)

ማኅበራዊ ሚዲያ ልንጠቀምበት የተፈጠረ እንጂ ሊገዛን የመጣ ዓለም ማድረግ የለብንም:: ይህን ነፃነታችንን በእጃችን የምንጠብቀው ራሳችን ነን:: ማኅበራዊ ሚዲያን እንዴት እንጠቀም ብለን ማሰብ እንጂ ከማኅበራዊ ሚዲያ ጋር መጣበቅም መራቅም ጉዳት አለው:: ማኅበራዊ ሚዲያን ከልክ ባለፈ በአግበስባሽነት መጠቀም ሱስ ወይም ልማድ ላልነው ተገዢነት ይዳርጋል:: መራቅ ደግሞ የምንኖርበትን ዓለም የመረዳትና በዚያ ሥርዓት ውስጥ ሕይወትን የመምራት ንቃተ ሕሊና ማጣትን ያስከትልብናል:: ስለዚህ በልኩና በአግባቡ ሆነን መጠቀምም ብልህነት ነው::

ማኅበራዊ ሚዲያ የጠቃሚነቱን ያህል ጎጂነቱም ብዙ ስለሆነ እንዴት መጠቀም እንዳለብን አስቀድሞ መወሰንም ብልህነት ነው:: በቀን ውስጥ ማኅበራዊ ሚዲያን ለመጠቀም የምናጠፋው ጊዜ ከሌላው በሕወታችን ልንፈጽማቸው ከሚገባቸው ጊዜ ሊበልጥ አሊያም ሌላውን ጊዜያችንን ሊሻማብን አይገባም:: በየዕለቱ የምንሠራቸውን ሥራዎች በዕቅድ ይዞ መከወኑ ከእንደዚህ ዓይነት የማኅበራዊ ሚዲያ ሱሰኝነት ሊያላቅቀን ይችላልና ቀናችንን በዕቅድ መምራትም ጠቃሚ ነው:: የሚጠቅመንን ስንፈልግ የሚያጋጥሙን ብዙ እኩይ ነገሮች በማኅበራዊ ሚዲያው ሾልከው ይመጣሉና ምርጫችንንም ማስተካከል ተገቢ ነው:: ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሊውል የሚገባው ጊዜያችንም በጊዜ ነቅቶ በከንቱ እንዳይባክን መጠንቀቁ ተገቢ ነው::

በተለይም እንደ አንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማኅበራዊ ሚዲያን ለምን አገልግሎት እንደምንፈልገው፤ መቼ መጠቀም እንዳለብን እንዲሁም ለምን ያህል ሰዓት የማኅበራዊ ሚዲያን መጠቀም እንዳለብን ወስኖ መጠቀሙ ለግልም ሆነ ለማኅበራዊ ሕይወታችን አዎንታዊ ለውጥ የሚያመጣ ነውና በዚህ መንገድ ልንበረታ ይገባል:: ከዚህም በተጨማሪ በማኅበራዊ ሚዲያ ምክንያት የሚደርስብንን መንፈሳዊ እና አካላዊ ጉዳት ይቀንሳል::

ከዚህ ሁሉ ርምጃ በኋላ ተሸናፊነት የሚሰማው ሰው በእግዚአብሔር ረድኤት ለማሸነፍ ጸሎትን በማዘውተርና የእግዚአብሔር ቃል አዘውትሮ በመስማት ድል መንሣት ይቻላል::

ውድ ጠያቂያችን ገብረ መድኅን በአጠቃላይ ማኅበራዊ ሚዲያን ያለገደብ የመጠቀም ነገር ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል በውል መገንዘብ፤ ከዚያም ማኅበራዊ ሚዲያን ለምንጠቀምበት መርሕ ወይም የሕይወት መመሪያ ታምኖ መኖር፣ ከልኩ በላይ የሚፈታተነን መሆኑን በተረዳንበት ልክ ራሳችንን የመግዛት ልምምድ ማድረግ፤ በሚያስፈልግ ጊዜም በልኩና ለአስፈላጊው ነገር ብቻ መጠቀም ተገቢ ነው:: ሲቦዝኑም ለሚሰማዎት ድብርት መሸሻም ተጨባጭ፣ ለመንፈስና ለሥጋ የሚጠቅሙ ሥራዎችን በመሥራት መትጋት፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችንንም ከዚህ ወሳኝ የሕይወት ተግባራችን ጋር አቆራኝቶ በጥንቃቄ መጠቀም ያስፈልጋል:: ከዚህ ባሻገር ግን እንደ ክርስቲያን የዘወትር ተግባራችን መሆን የሚገባው ጸሎትና ቅዱስ ቃሉን የመስማት ነገር ማብዛት መረሳት የሌለበት ነው::

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!***